አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ
የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ፤ በካፋ ዞን በተመረጡ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናሙናነት

በ

ተግባሩ መንገሻ

ሰኔ 2003 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ
የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ፤ በካፋ ዞን በተመረጡ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናሙናነት

በ

ተግባሩ መንገሻ

ሰኔ 2003 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ፤ በካፋ ዞን በተመረጡ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናሙናነት


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ
የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል


የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ. ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ


ተግባሩ መንገሻ



ሰኔ 2003 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

## የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

**የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ፤ በካፋ ዞን በተመረጡ ሶስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናሙናነት**

በ

ተግባሩ መንገሻ

ሰኔ 2003 ዓ.ም.

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ጌታሁን አማረ 10/10/03

አማካሪ ቀን ፊርማ

ጌታቸው እንግዳወርቅ 11/10/03

ፈታኝ ቀን ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቋ.ጥ.ተ. ቤተ መጻሕፍት ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

# ምስጋና

አማካሪዬ ዶ/ር ጌታሁን አማረ ይህንን ጥናት ከረቂቅ ጀምሮ ትክክለኛ አቅጣጫ በማመላከት እንዲሁም ያለምንም መሰልቸት ላደረጉልኝ ከፍተኛ እገዛ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

የጥናቱን ፅሑፍ ራሴ እንዳስተካክል የግል ኮምፒውተሯን በመስጠት ያገዘችኝ ከምንም በላይ ደግሞ የሞራል ብርታት በመሆን ጥናቱን እስካጠነቅቅ ከጎኔ የነበረች ውድ እህቴ ማርታ ሀብታሙ ውለታዋ ከምስጋና በላይ ቢሆንም ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረሳት፡፡

የክፍል ጓደኛዬ ይታያል ወርቁ እንዲሁም ጓደኛዬ ዱባለ ሳህለ በጥናቱ ሂደት ገንቢ አስተያየት በመስጠት ላደረጉልኝ እገዛ ምስጋናዬ የበዛ ነው፡፡

ለዚህ ስራ በአግባቡ መጠናቀቅ እገዛ ያደረጉልኝ ተቋማት አሉ፡፡ እነዚህም የቦንጋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የትምህርት ሙሉ ወጪዬን በመቻል ለዚህ ስላበቃኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡ እንዲሁም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለለምርምሩ የሚያስፈልገውን ገንዘብ በመስጠት ስለደገፈኝ አመሰግናለሁ፡፡

በመጨረሻም ለጥናቱ አጋዥ መረጃዎችን ለተባበሩኝ የጊምቦ ፣ የቢሻው ወ/ዮሐንስና የአውራዳ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራንና ተማሪዎች እንዲሁም ርዕሳነ መምህራን ላደረጉልኝ ቀና ትብብር ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

# ማውጫ

**ይዘት** ገጽ

ምስጋና ........ I
ማውጫ ........ II
የሠንጠረዥ ማውጫ ........ V
የአባሪ ማውጫ ........ VI
አጠቃሎ ........ VII
ምዕራፍ አንድ
1.መግቢያ ........ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2. የጥናቱ አላማ ........ 3
1.3. የጥናቱ ወሰን ........ 3
1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 3
1.10.ምህፃረ ቃላት ........ 4
ምዕራፍ ሁለት
2. ክለሳ ድርሳናት ........ 5
2.1. የማስተማሪያ ዘዴዎች አከፋፊል ........ 5
2.1.1. መምህር-ተኮር አቀራረብ ........ 6
2.1.2. ተማሪ-ተኮር አቀራረብ ........ 8
2.1.2.1. የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ገፅታዎች ........ 11
2.1.2.2. የተማሪ -ተኮር አቀራረብ ጠቀሜታ ........ 12
2.2. በተማሪ ተኮር አቀራረብ የተማሪውና የመምህሩ ሚና ........ 13
2.2.1. በተማሪ ተኮር አቀራረብ የተማሪው ሚና ........ 14
2.2.2. በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የመምህሩ ሚና ........ 15
2.3. የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ዘዴዎች ........ 17
2.3.1. ግኝታዊ የማስተማሪያ ዘዴ (Discovery Learning) ........ 18
2.3.2. የፕሮጀክት ዘዴ (Project Method) ........ 19

2.3.3. ትብብራዊ ትምህርት (Cooperative Learnig ........................................20
2.3.3.1. የትብብራዊ ትምህርት መርሆዎች ........................................20
2.3.4. የጥያቄ አቀራረብ ዘዴ (Questioning method) ........................................22
2.3.5. የቡድን ስራ (Group Work) ........................................23
2.3.5.1. የቡድን አመዳደብ አይነቶች (Kinds of grouping) ........................................23
2.3.6. የሚና ነጠቃ ዘዴ (Role Playing Method) ........................................24
2.3.7. ችግር ፈቺ ዘዴ (Problem solving methods) ........................................25
2.4. ተማሪ-ተኮር አቀረራብ ትግበራን ያደናቀፉ ችግሮች ........................................25
2.4.1. መምህራንና ተማሪዎች በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ላይ ያላቸው አመለካከት 25
2.4.2. የመማሪያ ክፍል ሁኔታ/classroom condition/ ........................................26
2.4.3. የተማሪዎች ብዛት /class size/ ........................................26
2.4.4. አካላዊ አካባቢ /physical environment/ ........................................26
2.4.5. በመማሪያ መፅሀፎችና በሞጁሎች ላይ ያለመካተት ........................................27
2.5 የቀደምት ስራዎች ቅኝት ........................................25
ምዕራፍ ሦስት
3. የጥናቱ ዘዴ ........................................29
3.1. የጥናቱ ተተኳሪዎች አመራረጥ ........................................29
3.1.1. የትምህርት ቤት አመራረጥ ........................................29
3.1.2. የምድብ አመራረጥ ........................................29
3.1.3. መምህራን ........................................31
3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ........................................31
3.2.1. የክፍል ውስጥ ምልከታ ........................................32
3.2.2. የፅሁፍ መጠይቅ ........................................32
3.2.3. ቃለ መጠይቅ ........................................33
3.3. የመረጃ አተናተን ስልት ........................................34
ምዕራፍ አራት
4. የመረጃ ትንተና ........................................35
4.1. የተማሪ-ተኮር የማስተማር ዘዴዎች አተገባበር ........................................35

4.2. በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የመምህራንና የተማሪው ሚና ....................................42
4.2.1. የመምህራን ሚና በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ....................................43
4.2.2. የተማሪው ሚና ....................................46
4.3. የመማሪያ ክፍሎች አደረጃጀት ....................................49
4.4. በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ....................................52
ምዕራፍ አምስት
5. ማጠቃለያና የመፍትሔ ሃሳብ ....................................56
5.1. ማጠቃለያ ....................................56
5.2. የመፍትሔ ሃሳቦች ....................................57
ዋቢ ጽሑፎች ....................................59
ሙዳየ ቃላት ....................................63
አባሪዎች ....................................65

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ አንድ፦ ትምህርት ቤቶቹና ያላቸው የምድብ ብዛት ....................................30

ሰንጠረዥ ሁለት፦ ለጥናቱ የተመረጡ ምድቦች ....................................................30

ሰንጠረዥ ሶስት፦ የተተኳሪ መምህራን አጠቃላይ መረጃ ....................................31

ሰንጠረዥ አራት፦ ከምልከታ የተገኘ መረጃ ..........................................................35

ሰንጠረዥ አምስት፦ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ ሁኔታ
/ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ/ .......................................37

ሰንጠረዥ ስድስት፦ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የመምህሩ ሚና /የምልከታ መረጃ/ ..43

ሰንጠረዥ ሰባት፦ የተማሪዎች ሚና ..........................................................................47

ሰንጠረዥ ስምንት፦ የክፍል አደረጃጀት....................................................................49

ሰንጠረዥ ዘጠኝ፦ ከምልከታ ቅፅ የተገኘ መረጃ ....................................................50

ሰንጠረዥ አስር፦ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ለመተግበር የሚገጥሙ ችግሮች ....53

# የአባሪ ማውጫ


አባሪ ሀ ........................................................................................................65

አባሪ ለ........................................................................................................67

አባሪ ሐ........................................................................................................70

አባሪ መ ......................................................................................................73

አባሪ ሠ ......................................................................................................76

አባሪ ረ ......................................................................................................77

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በካፋ ዞን በተመረጡ ሶስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያለውን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ መፈተሽ ነው። በትምህርት ቤቶቹ የአቀራረቡን አተገባበር ለመፈተሽ አጥኚው አሀዛዊና አይነታዊ የምርምር ዘዴዎችን ተከትሏል። መረጃዎችን ለመተንተን በአብዛኛው በአሀዝ የተጠቀመ ሲሆን በሰንጠረዥ ውስጥ የቀረበውን መረጃ እንዲሁም ከቃለመጠይቅ የተገኘውን መረጃ ለመተንተን ገለጻ ተጠቅሟል። በአሀዝ የቀረበው መረጃ በምልከታና በፅሁፍ መጠይቅ አማካይነት የተገኘ ነው። አጥኚው በካፋ ዞን ካሉት የመንግስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የጥናቱ ተተካሪዎች የሆኑትን ሶስት ትምህርት ቤቶች ለመምረጥ ተራ የዕጣ ንሞና የተጠቀመ ሲሆን ከትምህርት ቤቶቹ ተተኳሪ ምድቦን ለመለየት ደግሞ አመቺ ወይም ግኝታዊ ንሞና ለመጠቀም ችሏል። በተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች በመታገዝ የተሰበሰቡት መረጃዎች ተጠናቅረው የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው በጥቅሉ ሲታይ በትምህርት ቤቶቹ ተማሪ-ተኮር አቀራረብ በአግባቡ እየተተገበረ እንዳልሆነ ለመረጋገጥ ተችሏል። ለዚህም ምክንያቶቹ የጊዜ እጥረት ፣ የማመሪያ ክፍል ጥበት ፣ የተማሪዎች ብዛት ፣ የመማሪያ ክፍሎች አደራጃጀት አመቺ አለመሆን ፣ የተማሪዎች የተሳትፎ ፍላጎት ማነስ ፣ የመማሪያ መጻህፍት እጥረት እንዲሁም በመማሪያ ክፍል ውስጥ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተሟልቶ አላመገኘት ሆነው ተገኝተዋል። እነዚህን ችግሮች በመቅረፍ በትምህርት ቤቶቹ በአቀራረቡ የተሻለ ትግበራ እንዲኖር የመፍትሔ ሃሳቦችን በመጠቆም ጥናቱ ተጠናቋል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

የሰው ልጅ ቋንቋን በሁለት መንገዶች ሊያገኝ ይችላል፤ በመልመድ ወይም በመማር (Krashen 1987)፡፡ "መልመድ" አንድ ሰው ቋንቋን ተፈጥሮአዊ በሆነ ሂደት የሚያገኝበት ሲሆን ለመዳውም በከፊል እውቂያ (subconscious) እንዲሁም ኢ-መደበኛ በሆነ መልኩ የሚከወን ነው፡፡ "መማር" ግን በሙሉ እውቂያ (conscious) መደበኛ በሆነ መንገድ የሚከወን እንደሆነም ምሁሩ ገልጸዋል፡፡ የቋንቋ ትምህርት ተማሪው በመደበኛ አውድ ውስጥ የሚያከናውነውና እያንዳንዱን የቋንቋ ገፅታ ትኩረት በመስጠት የሚረዳበት መሆኑን ከምሁሩ ገለፃ መረዳት ይቻላል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረትም ይህንኑ የክፍል ውስጥ መደበኛ እና በሙሉ እውቂያ የሚከነውን የቋንቋ ትምህርት ሂደት መፈተሽ ይሆናል፡፡

የቋንቋ ትምህርት እንደጥበብና እንደሳይንስ ሲታይ ቆይቷል፡፡ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ጥበባዊነትና ሳይንሳዊነት በእኩል ደረጃ የሚንፀባረቁ እንደሆኑ እነ (Richards እና Rodgers 1986) ይገልፃሉ፡፡

የቋንቋ ትምህርት ጥበባዊነት መምህሩ የግል ተሰጥኦውን በመጠቀም የትምህርቱን ሂደት ሳቢና የሚጥም አድርጎ የሚያቀርብበት ሲሆን ሳይንሳዊነቱ ደግሞ የሚተገበር፣ ቀጣይነት ያለው፣ ውጤቱም የሚመዘን መሆኑ እንደሆነ (Clece-Murcia 1991) ገልጸዋል:: ስለዚህ በቋንቋ ትምህርት ሂደት እነዚህን ሁለት ገፅታዎች በጋራ ማስኬድ ተገቢ ነው፡፡ የቋንቋ መምህር አንድን ይዘት ለተማሪዎቹ ከማቅረቡ በፊት ስለቋንቋ ማስተማር ገፅታዎች ሊገነዘብና ሊያቅድ ይገባል፡፡

የቋንቋ ትምህርት ከጥበባዊነቱና ከሳይንሳዊነቱ ባሻገር በሁለት አበይት አቀራረቦች ሊከፈል ይችላል:: እነዚህም ተማሪ-ተኮር እና መምህር-ተኮር አቀራረቦች ናቸው፡፡ እነዚህን አቀራረቦች Moore (2001) ፣ Mc Combs (1997) ፣ Lue (2000) ፣ Kaplan (1990) እና Tudor (1996) እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡ መምህር-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ተለምዶዋዊና ዕድሜ ጠገብ የማስተማር ስልት ነው፡፡ በትምህርቱም

በአብዛኛው የመምህሩ የበላይነት ጐልቶ ይንጸባረቅበታል፡፡ ከዚህም የተነሳ ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ንቁ ተሳታፊ አይሆኑም ወይም ፍዝ ተመልካች ይሆናሉ፡፡ በአንጻሩ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ግንባር ቀደም ተሳታፊዎች ናቸው፡፡ ይህ አቀራረብ ተማሪዎች በአብዛኛው በራሳቸው ጥረት እንዲማሩ እድል ይሰጣል፡፡ አቀራረቡ ተማሪዎችን በብቃት የሚያሳትፍ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪው በትምህርቱ ሂደት መሪ ተዋናይ የሚሆንበትን እድል ይሰጣል፡፡ መምህር-ተኮር አቀራረብ ግን በአብዛኛው የመምህሩ የበላይነት ጎልቶ የሚታይበት ነው፡፡ ተማሪውን ንቁና ማእከላዊ ተሳታፊ ሳይሆን ፍዝ ተመልካች ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም ተማሪ-ተኮር አቀራረብ በተለይ ለቋንቋ ትምህርት ተመራጭ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪው ያለውን ውስጣዊ የቋንቋ ችሎታ በትምህርቱ ሂደት ማእከላዊ ተሳታፊ በመሆን እያዳመጠ፣ እየተናገረ፣ እያነበበ እና እየፃፈ የሚያሳድግበትን እድል ስለሚሰጥ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በኢትዮጵያ ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ አዲስ የትምህርት ፖሊሲ ተቀርፆ በስራ ላይ እየዋለ ይገኛል (ት.ሚ 1994)፡፡ ሆኖም ይህ ተማሪ-መራሽ ዘዴ በፖሊሲ ደረጃ በትምህርት ስራ ላይ ቢውልም የአተገባበር ችግሮች እንዳሉት ሙሉጌታ (1996) ፣ ኤልያስ (1997)፣ Fisseha (2001) በቀደሙት ጥናቶቸው ጠቁመዋል።

በአንጻሩ የዚህን ጥናት አቅራቢ ለዚህ ጥናት ያነሳሱት ምክንያቶች ከሚሰራበት ተቋም ውስጥ በከፍተኛ ዲፕሎማ ስልጠና ስለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ያገኘው ግንዛቤ ሲሆን ሌላው በሁለተኛ ዲግሪ ስልጠና ወቅት ከቋንቋ መማርና ማስተማር ትውረቶች ኮርስ ያገኘው ግንዛቤ ነው፡፡ ካፋ ዞን አጥኚው ቀደም ሲል የተማረበት እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ስራ የሚሰራበት ቦታ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ቦታ የመረጠበት ምክንያት በተለያዩ ምክንያቶች ከመምህራንና ከተማሪዎች እንዲሁም ከርዕሰ መምህራን ጋር ስለሚግባባ ለጥናቱ የተሻለ መረጃ ለማግኘት ሲባል ነው፡፡ በዚህም በመሠረት አጥኚው የሚከተሉትን ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ በጉዳዩ ላይ ጥናት አካሂዷል፡፡

- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ስልት ተጠቅመው ምን ያህል እያስተማሩ ይገኛሉ?
- መምህራን ተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ሲጠቀሙ የሚገጥሟቸው ችግሮች ምንድን ናቸው?
- ለችግሮቹስ መፍትሂዎች ምን ምን ናቸው?

## 1.2. የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በካፋ ዞን በተመረጡ ሶስት የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ እና 10ኛ) ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪ-ተኮር ተስተምህሮ አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡ ይህንን አጠቃላይ አላማ መሰረት በማድረግ ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር አለማዎች ይኖሩታል፡፡

- በካፋ ዞን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ምን ያህል እየተጠቀሙ እንደሚገኙ መለየት፡፡
- ተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብን ሊያደናቅፍ የሚችሉ ችግሮችን መለየት፡፡
- ችግሮቹን ለመቅረፍ የሚያስችሉ የመፍትሔ ሃሳቦችን መጠቆም፡፡

## 1.3. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የተካሄደው በካፋ ዞን በተመረጡ ሶስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በዞኑ የሚገኙት የመንግስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አስራ አንድ ሲሆኑ ጥናቱ በሶስቱ ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ ተወስኗል። በተጨማሪም በመማር ማስተማር ሂደት በርካታ ጉዳዮች ያሉ ቢሆንም ይህ ጥናት ግን በተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ አተገባበር ፍተሻ ላይ ብቻ ያተኮረ ነው። ሆኖም በጥናቱ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ለማካተት ከአቅም ፣ ከጊዜና ከወጭ አንጻር የማይቻል ከመሆኑም በላይ በጥናቱ ሂደት ሊከሰቱ የሚችሉ ተላውጦዎችን ለመቆጣጠር አዳጋች ስለሚሆን ነው።

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ውጤቱ ተጠቃልሎ ሲታወቅ የሚከተሉት ጠቀሚታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- ተማሪ-ተኮር የማስተማር ዘዴ ለቋንቋ ትምህርት ያለውን ፋይዳ ይጠቁማል
- በአቀራረቡ ዙሪያ ጠቃሚ ሀሳቦችን በማንሳት የቋንቋው መምህራን ስለተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ዘዴ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያስችላል፡፡

- በካፋ ዞን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለጊዜ የተማሪ-ተኮር የማስተማር ዘዴዎች አጠቃቀም አንጻር ያለውን ሁኔታ ይጠቁማል፡፡
- በጉዳዩ ላይ ቀጣይ ጥናት ለሚያደርጉ እንደመነሻ ይሆናል።

## 1.5. ምህፃረ ቃላት

ICDR – Institute of Curriculum Development and Research

ኮመትኮ - ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ

ደማመትኮ - ደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ከተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ጋር የሚዛመዱ ዕሑፎች ይቃኛሉ፡፡ በተለይም በምዕራፉ የተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብን ምንነት ፣ የተማሪ-ተኮር የማስተማር ዘዴ አይነቶች፣ አተገባበር እንዲሁም ትግበራውን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ችግሮች በዝርዝር ይቃኛል።

### 2.1. የማስተማሪያ ዘዴዎች አከፋፈል

የማስተማሪያ ዘዴዎች ከተለያየ አንጻር በተለያየ አይነት ሊከፈሉ ይችላሉ። (Mutassa and Wills 1994) እና (ICDR 1999) የተለያዩ ተመራማሪዎች የተለያዩ አከፋፈሎችን እንደሚጠቀሙና እነዚህም አከፋፈሎች አንዱን ከሌላኛው ለመለየት አስቸጋሪ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ቀጥሎ የተጠቀሱትም ከእነዚህ የሚመደቡ ናቸው፡፡

- መምህር-ተኮርና ተማሪ-ተኮር (Teacher Centered Vs student Centered)
- ቀጥተኛ እና ኢ-ቀጥተኛ (Direct instruction Vs indirect instruction)
- ጥንታዊ እና ዘመናዊ (Traditional Vs Modern Instruction)
- ልማዳዊና ልማዳዊ ያልሆነ (Conventional Vs Non Conventional )

ከፍ ሲል የተዘረዘሩት የማስተማሪያ ዘዴ አከፋፈሎች ምንም እንኳን በተለያየ መልኩ ቢገለጹም በአብዛኛው ተመሳሳይ አስተሳሰብ ያላቸው ናቸው፡፡ እነዚህ የተለያዩ አከፋፈሎች በትምህርቱ ሂደት ውስጥ ያለውን የተማሪው የተሳትፎ ደረጃ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት (Capel, et al 1995) እንደገለጹት ቀጥተኛ እና ኢ-ቀጥተኛ የተባለው አከፋፈል፤ ቀጥተኛ (መምህር-ተኮር፣ ጥንታዊ ፣ መደበኛ፣ ማብራሪያ ሰጪ፣ መምህሩን ብቻ ፈላጭ ቆራጭ የሚያደርግ) ፣ ኢ-ቀጥተኛ (ተማሪ-ተኮር፣ ዲሞክራሲያዊ፣ አሳታፊ፣ ኢ-መደበኛ ወዘተ...) በማለት የሚከተሉትን ነጥቦች መሠረት በማድረግ ገልጸዋል።

1. የዕውቀት ምንጭ፦ የዕውቀቱ ማዕከል ወይም መሠረት ማን ነው?
2. የመምህሩ ሚና፦ የመምህሩ ሚና ማመቻቸት ነው ወይስ መረጃ መስጠት?
3. የተማሪው፦ ተማሪው ንቁ አድማጭ ነው ወይስ ንቁ አድራጊ?
4. የምዘና ሁኔታ፦ የምዘናው ስርዓት ተጨባጭ ነው ወይስ አይደለም?

ይህ የሚያመለክተው በአጠቃላይ የዘዴዎቹ አከፋፈል በስም የተለያየ ቢሆንም በጽንሰ ሐሳብ ግን ተመሳሳይ መሆናቸውን ነው፡፡ ምክንያቱም አከፋፈሎቹ መምህሩና ተማሪው በትምህርቱ ሂደት ላይ የሚኖራቸው ሚና ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸው ነው። በመሆኑም እነዚህን ዘዴዎች በሁለት መልኩ ብቻ ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ እነዚህም መምህር-ተኮር እና ተማሪ-ተኮር የሚባሉ ዘዴዎች ናቸው፡፡ ቀጥለን ሁለቱን የትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች በዝርዝር እናያለን።

### 2.1.1. መምህር-ተኮር አቀራረብ

ይህ አቀራረብ ሀላፊነቱንና ቀዳሚውን ሚና ለመምህሩ ይሰጣል፡፡ መምህሩ የክፍል ውስጥ ክንውን ማዕከል እና መምህሩ ለተማሪው በአብዛኛው እውቀት ሰጪ እንዲሆን ይታሰባል፡፡ ICDR (1999:68) ፣ Mutassa and Wills (1994) ፣ Eggen and Kauchax (1996:180) የመምህር-ተኮር አቀራረብን እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡ “በመምህር-ተኮር ትምህርት የመማሪያ ክፍሉ መምህር መሪሽ የሆነና ቅደም ተከተሉን ጠብቆ የቀረበ እንዲሁም የቀለም ትምህርት ላይ ትኩረቱን ያደረገ ነው፡፡ በዚህ አቀራረብ ለማስተማሪያ የሚሰጠው ጊዜ በቂና ቀጣይ፣ የሚቀርበው ይዘት ሰፊ፣ የተማሪው ግንዛቤ የተወሰነ ነው፡፡ ከምንም በላይ መምህሩ ይዘትን በማዋቀር፣ በመግለጽና የተማሪዎችን ግንዛቤ ለመጨመር የተለያዩ ምሳሌዎችን በመንቀስ ቀዳሚውን ሚና ይጫወታል”። መምህር-ተኮር አቀራረብ መምህሩ በትምህርቱ ሂደት ቀዳሚውንና አብዛኛውን ሚና እንዲወጣ የሚያደርግ እንደሆነ ከፍ ሲል ከቀረበው የምሁራን ገለፃ መረዳት ይቻላል። ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ተግባብተው እንዲማማሩ ከማድረግ ይልቅ ተማሪዎች እንዲማሩት የተፈለገውን መረጃ ሙሉ በሙሉ መምህሩ እንዲሰጥ የሚያደርግ አቀራረብ ነው፡፡

(Borich 1984) ይህንን ሀሳብ እንደገለጹት በዚህ አቀራረብ መምህሩ ለትምህርቱ ሂደት መሪና መምህሩ ሁሉን አዋቂ እንደሆነ ይታሰባል፡፡ መምህሩ በትምህርቱ ሂደት

አብዛኛውን ሚና ይወስዳል፡፡ በአንጻሩ ተማሪውን እንደ “ባዶ ዕቃ”ና መምህሩ የሚሞላ ተደርጎ ይታሰባል (Plass 1998) ፣ (Lue 2000፡10)።

በዚህም ምክንያት መምህሩ በአብዛኛው ሰጪና የተማሪዎቹም ግዴታ መቀበል ፣ መምህሩ የነገራቸውን ማስታወስ እንዲሁም ጥያቄ መመለስ ወይም በፈተና ጊዜ ጽሑፍ መስጠት ይሆናል (Eggen and Kauchax 1996:179)::

በ(ICDR 1999:68) ውስጥ እንደተመለከተው በዚህ የማስተማሪያ ዘዴ መምህሩ የሚጠቀመው ጠመኔና ንግግር (Chalk and Talk) ወይም መምህሩን ብቻ ራሱን ንቁ የሚያደርጉ ፣ ተማሪዎችን ግን ፍዝ አድማጭ ሆነው እንዲቀዩ የሚያደርጓቸውን ዘዴዎች ይጠቀማል። መምህሩ ተማሪዎቹ ከሰሌዳ ወደ ደብተራቸው የሚገለብጡትን ጽሑፍ ወይም በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ያለውን መረጃ ማስታወሻ እንዲወስዱ ያደርጋቸዋል። በትምህርቱ አቀራረብ አብዛኛው የስራ ድርሻ የመምህሩ ነው። ተማሪዎች ደግሞ መምህሩ ያላቸውን ብቻ የሚያዳምጡ፣ የገፈላቸውን ብቻ የሚያነቡ፣ በአጠቃላይ የትምህርቱ ሂደት በመምህሩ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ አካሄድ ይከተላሉ። (Macharia and Waria 1994:39) የመምህር-ተኮር አቀራረብን መሠረታዊ ባህሪያት እንደሚከተለው በአጭሩ ገልጸውታል ፡፡

- መምህሩ ከተማሪው ይበልጥ ንቁ ተሳታፊ ነው።
- መምህሩ በገለጻ ፣ ቁጥጥር እና በማብራራት ረገድ ንቁ ነው።
- መምህሩ በሚያስተምርበት ጊዜ ተማሪዎቹ ፍዝ አድማጮች ናቸው፡፡
- የተማሪዎች መቀመጫ ወንበሮች በዙር ሳይሆን በቀጥታ የተደረደሩ ናቸው፡፡
- የተማሪዎቹ ዋና ተግባር በዝምታ ማዳመጥና ከሰሌዳ ላይ ጽሑፍ መገልበጥ ነው።
- የቡድን ስራ የለም።

(Plass 1998) የቀጥተኛ ወይም የመምህር-ተኮር አቀራረብን ውጤት እንደሚከተለው ጠቅሰዋል፡፡ በአብዛኛው ተማሪዎች የሚማሩት ትዕዛዝ መቀበልን፣ መስማማትን እንጂ በክፍል ውስጥ በትምህርታቸው አማካይነት በእለት ተእለት ህይወታቸው ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች አይፈቱበትም። በመሆኑም መምህር መራሽ የማስተማሪያ

ዘዴዎች ተማሪዎችን በሕይወታቸው ውስጥ ያሉትን ተለዋዋጭ ሁኔታዎች እንዲቋቋሙ የሚያስተምሩ ሳይሆኑ ግትርና የመምህሩን ሃሳብ ብቻ እንዲቀበሉ ወይም እንዲኮርጁ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ መምህር-ተኮር ክፍለ ጊዜ ተማሪዎችን ፍዝ የእውቀት ተቀባይ ያደርጋቸዋል፡፡ የትምህርቱ ሃላፊነት በተማሪው ላይ ሳይሆን በመምህሩና በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ የመምህር-ተኮር አቀራረብ ከተግባራዊ ትምህርት ይልቅ በንድፈ ሃሳብ ላይ ያተኩራል፡፡ በመሆኑም ተማሪው እየተገበረ የሚለማመድበትን እድል አይፈጥርም። ትምህርቱ በተማሪው ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን መምህሩ በፈለገው መንገድ የሚያዘጋጀውና የሚያስተምረው በመሆኑ ተማሪዎች ለትምህርቱ ተነሳሽነት እንዲሁም ትኩረት ዝቅተኛ ይሆናል።

### 2.1.2. ተማሪ-ተኮር አቀራረብ (Student centered Approah)

ስለተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ምሁራን ከጥንታዊ ወይም መምህር- ተኮር ጋር እያነጻጸሩ ያብራራሉ፡፡ (Brad 2000፡179) ሁለቱን የትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች እያነጻጸሩ እንደሚከተለው ገልጸዋል::

> *በጥንታዊው የማስተማር ሂደት ተማሪዎች እንዲማሩ የሚፈለገው ነገር ከመምህሩ ሙሉ በሙሉ ይተላለፍላቸዋል፡፡ በመሆኑም የተማሪዎቹ ተሳትፎ ፍዝ ይሆናል። ነገር ግን በተማሪ-ተኮር የትምህርት ሂደት ተማሪዎች በትምህርታቸው ላይ በንቃት የሚሳተፉና በትምህርቱም ማዕከላዊ ተሳታፊዎቹ ተማሪዎች ሲሆኑ መምህሩ በአብዛኛው አቅጣጫ የማሳየት ስራ ይሰራል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በዚህ አቀራረብ ክሂሎችን ለማዳበር ይማራሉ፡፡ ከፍዝ አድማጭነት የተሻለ ጥልቅ እውቀት ያገኙበታል፡፡*

በተመሳሳይ(www.neiu.edu./.dbehlrhe/hrd408/glossery.htm)ላይ እንደተገለጸው በተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን እንደ ባዶ ጭንቅላት በማሰብ ዕውቀትን ፍዝ በሆነ መንገድ ለተማሪዎች ከማፍሰስ ይልቅ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን ወደ ሚያከናውኑበትና በአብዛኛው እንቅስቃሴ ወዳለው አመለካከት ቀይሮታል። በዚህ ምክንያት ተማሪዎች አዲስ ዕውቀትን በመፍጠር ለሌሎች ሙያዎችና ለትምህርት በጣም ጠቃሚ ሚና ይጫወታሉ። ከዚህ በተጨማሪ እንደ እነ (Bonwell and Elison 2003:38) ገለጻ አሳታፊ አቀራረብ ተማሪዎችን ፍዝ ተቀባይ ከማድረግ ይልቅ በትምህርቱ ሂደት ንቁ ተሳታፊ ያደርጋቸዋል::

የምሁራኑ ገለፃ እንደሚያስረዳው ተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተማሪዎችን በትምህርቱ ሂደት ማዕከላዊ ወይም መሪ የሚያደርግ የማስተማር ሂደት ነው፡፡ (Tudor 1996) በበኩላቸው ተማሪ-ተኮር አቀራረብ ማለት ተማሪዎቹን የትምህርቱ ማዕከል ማድረግ ነው፤ ብለዋል፡፡

ተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተማሪ መሪሽ በመሆኑ ለተማሪዎች ሙሉ በሙሉ የመማር ነፃነት ይሰጣል፡፡ የትምህርቱም ሂደት የተማሪውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ይሆናል:: ይህን አስመልክቶ (Reed and Bergeman 1995) ሲገልጹ "የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ማለት ለተማሪዎች የመጨረሻውን የመማር ነፃነት የሚሰጥ ነው፡፡ መምህራኑ ደግሞ ለተማሪዎቻቸው ትክክለኛና ተገቢ የሆነ የመማር ማስተማር አውድና የማስተማሪያ ምንጭ በመፍጠር የልጆችን እድገት የሚያፋጥኑበት ነው፡፡ የማስተማሩ ብልሃትም የተማሪዎችን ፍላጎት መሰረት አድርጎ የተዘጋጀውን ትምህርት ማቅርብ ነው፡፡ ይህ አቀራረብ በአካል ወይም በአእምሮ ጉዳተኛ የሆኑ ተማሪዎችን ሳይቀር እድገታቸው ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ እንዲከናወንና በመማሪያ ክፍሉም ውስጥ ውጤታማ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያስችል የክፍል አያያዝ ወይም አስተዳደር የሚታይበት ነው፡፡

ሙሉጌታ 1996 ፣ አቀራረቡ በተማሪዎች አመለካከትና ስኬታማነት ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ከዚህ ሌላ የተለያየ ጎሣና ብሔር ባላቸው ተማሪዎች መካከል በአመለካከት፣ በእድገትና አጠቃላይ በሆነ ስኬታማነት ረገድ ውጤታማ የሆነ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ ተማሪዎችም የራሳቸውን ባህል ዳራና የሕይወት ልምድ ለማበልጸግ ይበረታታሉ፡፡ መምህራኑም የተማሪዎችን የመማር ሂደት ከመምራት ታቅበው ተማሪዎች በራሳቸው ስለራሳቸው ትምህርት እንዲወያዩ እንዲሰሩና የራሳቸውን ጥናትና ምርምር ለማከናወን እንዲተጉ የሚበረታቱበት መድረክ ነው፡፡ ይህ ማለት በጣም አስፈላጊው የመማር ማስተማር አካል ተማሪዎችን በትምህርቱ ስራ ላይ ጣልቃ ማስገባት ወይም ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ነው (Reed and Bergemann 1995)።

እንደነ (Bonwell and Elison 2003:106) ገለጻ ተማሪዎች ከሚያዳምጡት ይልቅ የሚያደርጉት መብለጥ አለበት፡፡ ተማሪዎች ማንበብ፣ መጻፍ ፣ መወያየትና ችግሮችን በመፍታት ሂደት ውስጥ ማእከላዊ ተሳታፊ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በመሆኑም በዚህ ዘዴ

ተማሪዎች በማድረግ ይማራሉ፡፡ ይህ የሚያመለክተው የተማሪዎቹ ትምህርት የሚወሰነው በሚሰሩት ስራ ይሆናል።

በአጠቃላይ የመማር ማስተማሩን ሂደት ንቁ ለማድረግ የሚከተሉትን መሠረታዊ ነጥቦች ከግምት ውስጥ መግባት እንዳባቸው በ (ICDR 1999:93) ውስጥ ተገልጿል::

- መማር ውጤታማ የሚሆነው ተማሪዎች መጠቀም ሲችሉ፣ ትምህርታቸውን ከዕለት ተዕለት ህይወታቸው ጋር ሲያቆራኙ፣ በትምህርታቸው ውስጥ በንቃት ሲሳተፉ ብቻ ነው፡፡

- ውጤታማ ትምህርት እውነታዎችን ማስታወስና የዕውቀት ዝርዝር አይደለም፡፡

- እውነታዎችን ብቻ መማር ተማሪዎችን ነገሮች በጥልቀት ለመገንዘብና በዚህ ውሰብስብ አለም ውስጥ ለመሳተፍ አያዘጋጃቸውም፡፡

- መማር ተማሪዎች ችግሮችን እንዲፈቱ ፣ በአካባቢያቸው ያለውን መረጃ እንዲጠቀሙና ለራሳቸው፣ ለቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ለማህበረሰባቸው የተሻለ ህይወት እንዲፈጥሩ ያዘጋጃል፡፡

- ተማሪዎች ከተለያየ አመለካከት ወይም አቅጣጫ እንዲገነዘቡና ብዙ ግብአቶችን እንዲያገኙ ከአንድ በላይ የመረጃ ምንጮችን ልንሰጣቸው ይገባል፡፡

- ተማሪዎች ስለሚማሩትና ስለሚሰሩት ነገር ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲገልጹ ማበረታታት አለብን።

- ተማሪዎችን የሚጠቅሙ ችግሮችን ማንሳት አለብን፡፡ በተማሪዎች ፍላጐት ላይ በመመስረትና የተማሪዎችን ቀደምት ዕውቀት መነሻ በማድረግ ተማሪዎች ለትምህርቱ እንዲቀሰቀሱና እንዲነሳሱ ማድረግ፣ ለተማሪዎች አስፈላጊ ጥያቄ ማቅረብ ያላቸውን አስተሳሰብና ግንዛቤ አውጥተው እንዲጠይቁ ይገፋፋቸዋል፡፡

- ትምህርትን ከቀዳማይ ፅንሰ ሀሳቦች ተመስረተን ማዋቀር አለብን፡፡ ይህም የሚያመለክተው ተማሪዎችን ለተቆራረጡና ተያያዥነት ለሌላቸው ማለትም እርስ በራሳቸው ሊገናኙ ከማይችሉ ሀሳቦች ከማጋለጥ ይልቅ የትምህርቱን ዝርዝር ይዘቶች በዋናው ሀሳብ ዙሪያ መገንባትን ነው፡፡

#### 2.1.2.1. የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ገፅታዎች

በዚህ አዲስ በሆነው የተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራርብ ዘዴ ተማሪዎች መረጃን ከመምህራቸው በቀጥታ አይቀበሉም። በተቃራኒው ትምህርታቸውን ከዕለት ተዕለት ህይወታቸው ጋር ያነፃፅሩታል፣ ይወያዩበታል፣ ይተነትኑታል፣ ማጠቃለያ ያወጡለታል፣ ይግባቡበታል (ICDR 1999:71)። ተማሪዎች መምህራቸው ከሚሰጣቸው የመረጃ ምንጮች እንዲሁም ከመማሪያ መፅሀፎች በሚያገኟቸው መነሻዎች በንቃት ለመስራት፣ ለመጠየቅ ፣ መረጃዎቹን መሠረት በማድረግ ለመፍጠር ፣ መረጃውን ለመተንተን፣ ስለ መረጃው በጥልቀት ለማሰብና ዘገባ ለማዘጋጀት ጥረት ያደርጋሉ (Aggrawal 1996)።

በተመሣሣይ ሁኔታ (Squazzin and Graan 1998:57) ሲገልፁ ተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ማህበራዊ ሂደትና የዚህም ሂደት ትኩረት የተለያዩ ሰዎችን ማገናኘትና እነዚህ ሰዎች ሀሳቦችን፣ ልምዶችን፣ አመለካከቶችን ወዘተ እንዲለዋወጡ የማድረግ ሂደት ነው። አቀራረቡ ከሌሎች ጋር በመግባባትና በንቃት በመሣተፍ ተማሪዎች ግንዛቤያቸውን እንዲያሳድጉ ያግዛቸዋል። በዚህ ሂደት ተማሪዎቹ የትምህርቱ ማዕከል ይሆናሉ (Lue 2000:4)። እነ (Eggen and Kauchax 1996:83) በበኩላቸው ተማሪውን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ማዕከላዊ ተሳታፊ ያደርጉታል።

> *የወቅቱ ጥናታዊ ምርምሮች ትኩረት በተማሪ ሚና ላይ ነው። ይህም የሚያተኩረው ተማሪዎች በትምህርታቸው ሂደት ፍዝ በሆነ መንገድ ከመምህሩ መረጃ መቀበል ወይም መገልበጥ እንደሌለባቸው የሚያሳይ ነው። በአንጻሩ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት በንቃት እንዲሳተፉና የተማሩትን ይዘት ቀድሞ ከነበራቸው ግንዛቤ ጋር እንዲያዛምዱ ማድረግ ነው። በዚህም መሠረት ተማሪዎች በንቁ ተሳትፎ ሂደት አዲስ ዕውቀት ያዳብራሉ።*

ከላይ የቀረበውን ሀሳብ በማጠናከር (Plass 1998:312) እንደሚገልፁት በአሳታፊ አቀራረብ የቀደሙት ዕውቀትና ልምዶች አዲስ ዕውቀት ለመገንባት ስለሚረዱ ጠቃሚና መሠረታዊ ናቸው። የመምህሩ ሚና ለተማሪዎች ምቹ የትምህርት አካባቢ መፍጠርና አቅጣጫ ማሳየት፣ ማስተባበር፣ መመልከትና መገምገም ነው። በሌላ አገላለፅ መምህሩ እንደ አስተባባሪ አብሮ መስራት እንጂ መረጃ መስጠት ብቻ

አይጠበቅበትም፡፡ ነገር ግን በክርክር በውይይት፣ በፈጠራ፣ በገለፃ ወዘተ ተማሪዎች ለመገንዘብ የሚማሩበትን አቀራረብ ይቀርፃል፡፡

### 2.1.2.2. የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ጠቀሜታ

ተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች በአብዛኛው በጋራ እንዲሰሩ እድል ስለሚሰጥ ለትምህርት ሂደት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ይህን አስመልክተው እነ (Bonwell and Elison 2003:66) እንደገለጹት ተማሪ-ተኮር ትምህርት በተማሪዎች መማር ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስላለው በትምህርቱ ሂደት መሠረታዊ ነው፡፡ በተጨማሪም በርካታ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከጥንታዊ የትምህርት አቀራረብ ይልቅ አሳታፊ የሚያደርጉ ብልሀቶችን እንደሚመርጡ ይገልጻሉ። በተጨማሪም http://www. honolulu.hawail.edu, ውስጥ እንደተገለፀው አሳታፊ አቀራረብ በትምህርቱ ሂደት የሚኖረውን የተማሪዎች ተሳትፎ ሊያሳድግ የሚችል ብልሃት ነው፡፡ ብዙ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አሳታፊ የትምህርት አቀራረብ የተማሪ ትምህርት ቤት ግንኙነት፣ የተማሪ ተማሪ ግንኙነት፣ የትምህርት ውጤት የተግበቦት ክሂሎችን፣ የከፍተኛ ደረጃ የአስተሳሰብ ክሂሎችን፣ የቡድን ስራን፣ በትምህርቱ ላይ ያለውን አመለካከት እና የመማር ተነሳሶት ያሳድጋል፡፡ ስለዚህ ቀደም ሲል እንደተገለጸው አሳታፊ የትምህርት አቀራረብ ተማሪዎችን ከፍዝ ተቀባይነት በትምህርታቸው ሂደቶች የራሳቸው ሚና ወደ አላቸው ተሳታፊዎች እንዲቀየሩ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት አሳታፊ አቀራረብ የተግባራት ወይም እንቅስቃሴዎች ስብስብ ብቻ ሳይሆን የመምሩና የተማሪዎቹ ትምህርትን ውጤታማ የማድረግ አመለካከት ነው፡፡ በይበልጥ ሲዘረዝር "የአሳታፊ አቀራረብ አላማ ተማሪዎችን ለረጅም ጊዜ ግንዛቤ ተማሪዎች እንዴትና ምን እየተማሩ እንደሆነ እንዲያስቡና በከፍተኛ ሁኔታ በትምህርታቸው ተጠያቂነት እንዲሰማቸው ማነቃቃት ነው (Silberman 1996:32)፡፡

ውጤታማ ትምህርት እውን ለማድረግ ተማሪ-ተኮር ዘዴዎችና የተለያዩ ክፍል ውስጥ ተግበራት ጠቃሚ ናቸው፡፡ ምክንያቱም በ (ICDR 1999:66) እንደተገለጸው:-

- ንቁና ተሳታፊ ስንሆን የበለጠ እናስታውሳለን።
- ንቁ ስንሆን ይበልጥ ግልፅ እንሆናለን።

- አሳታፊ ትምህርት በተለይ ለወጣት ተማሪዎች በአብዛኛው አስፈላጊ ነው።
- ወጣት ተማሪዎች ትምህርታቸውን ከህይወታቸው ከተማሩት ጋር ካገናኙ የተሻለ ይማራሉ፤ ትርጉምም ያለው ይሆናል፡፡
- ነገሮችን ለማስታወስ ከመማር ይልቅ ለማወቅና ለማሰብ መማር የተሻለ ነው።
- አሳታፊ ትምህርት የረዥም ጊዜ እውቀት ያስገኛል።
- አሳታፊ ትምህርት መሳተፍን ፣ መተንተናንን ፣ መሄስን ስለሚያበረታታ ተማሪዎች ከፈተተኛ የአስተሳሰብ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ያግዛቸዋል።
- ተግባራት ውጤታማ ትስስር ለመፍጠር ይረዳሉ፡፡
- አሳታፊ አቀራረብ ተማሪዎች በዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ውስጥ እንዲሳተፉ ያዘጋጃቸዋል፡፡

(Chet et.al 1993:81) በበኩላቸው ውጤታማ የመማር ሂደትን እውን ለማድረግ ተሳትፎ መሠረታዊ ጉዳይ እንደሆነ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

> *"እውነተኛ ትምህርት ማስታወስ አይደለም፡፡ የምናስታውሳቸው ነገሮች በአብዛኛው በቀላሉ የሚረሱ ናቸው፡፡ መማር የተማርነውን በማስታወስ ሁሉንም መሰብሰብ ሊሆን አይችልም ተማሪዎች ሊያብላሉት ይገባል፡፡ መማር የሚመጣው በስሜቶች አማካይነት በተለያዩ አይነት ሁኔታዎች ውስጥ በመጋለጥ ነው፡፡ ትምህርቱ አሳታፊ በሚሆንበት ጊዜ ተማሪዎች ጥያቄዎችን በመመለስ የሆነ ነገር ያገኛሉ፣ ችግር ለመፍታት መረጃ ያገኛሉ፣ ወይም ስራ ለመስራት አቅጣጫ ያገኛሉ፡፡ ተማሪው ከሌሎች ጋር የሚያደርገው ውይይት እንዲረዳና በከፍተኛ ደረጃ እንዲማር ያስችለዋል/ላታል፡፡*

በማለት ተማሪ-ተኮር አቀራረብ በተማሪዎች የመማር ሂደት ውስጥ እጅግ ጠቃሚ መሆኑን ገልጸዋል።

## 2.2. በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የተማሪውና የመምህሩ ሚና

(Garkns and Redman 1986)ን ጠቅሶ ሙሉጌታ ይታየው (1996:36) እንደገለፀው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመጣው የመማር ማስተማር ብልሃት የራስን ማስተማሪያ ማዘጋጀት የሚልና የክፍል ውስጥ አወቃቀሩና አደረጃጀቱም በመምህሩ ላይ ከሚያተኩረው ይልቅ ተማሪውን ማዕከል በሚያደርገው ተግባር ላይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች በራሳቸው ትምህርት ላይ ሀላፊነቱን እንዲወሰዱ ብቻ ሳይሆን የግለሰቦችንም

ፍላጐት ከግምት ውስጥ ያስገባል፡፡ከምሁራኑ ገለፃ የምንረዳው ጥንት የነበረው የመምህር-ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት ተምረው እውቀት እንዲያገኙ ካለማድረግም ባሻገር የተማሪዎች ፍላጎት ላይ የተመሠረተ አልነበረም፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጀመረው ተማሪ-ተኮር አቀራረብ ግን ተማሪውን ማዕከል ያደረገና አብዛኛው የስራ ድርሻ የሚወጣው ተማሪው በመሆኑ ነገሮችን በጥልቀት እንዲገነዘብ ያደርገዋል፡፡ በክፍል ውስጥ የሚኖረውም ክንውን የተማሪዎችን ፍላጎት መሠረት የሚያደርግ በመሆኑ ትምህርቱን ሳይሰለቹ ይከታተላሉ፡፡ በመሆኑም በዚህ ለተማሪ እንቅስቃሴ ትኩረት በሚሰጠው ተማሪ-ተኮር አቀራረብ የሁለቱን አካላት ማለትም የመምህራንና የተማሪውን ሚና በዝርዝር ለማየት ይሞከራል፡፡

### 2.2.1. በተማሪ ተኮር አቀራረብ የተማሪው ሚና

(Nunan 1989) በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች የሚኖሯቸውን ሚናዎች እንደሚከተለው ዘርዝረውታል፡፡

- ተማሪዎች በመረጃ መሣሪያ ዝግጅት አጠቃቀም ላይ የላቀ ተሳትፎ ያደርጋሉ.
- የተማሪዎች ሚና ከመምህሩ ተግባርና ደረጃ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው፡፡
- በአቀራረቡ ተማሪዎች ለውስጣዊ ንሺ ለዘብተኛ ተቀባይ ናቸው፡፡
- በመስጠትና በመቀበል ላይ መስተጋብርና ስምምነት ይለምዳሉ፡፡
- ከአድማጭነት ባሻገር በትምህርቱ ይዘት ላይ በጥቂቱም ቢሆን ቁጥጥር ማድረግ ይችላሉ፡፡
- በትምህርቱ በግላዊ ዕድገታቸው ላይ ሀላፊነት እንዲወስዱ ያደርጋቸዋል፡፡
- በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይጠበቃሉ፣ በዚህም የተማሪዎች የርስበርስ ሚና እና ስነ-ልቦናዊ የማስተማር ሂደት መለያየቱን ይገነዘባሉ፡፡
- ተማሪዎች ትምርታቸውን እንዴት መማር እንዳለባቸው የሚያስችላቸውን ነፃነትና ክሂል ያዳብራሉ፡፡

- ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎች ከሁኔታዎች ጋር የመስማማት ክሂሎችን፣ የፈጠሪነት ችሎታን፣ የመፈላሰፍ ጥበብንና በሁሉም ነገ መሆንን ይለምዳሉ፡፡

ሙሉጌታ (1996) (Dickison 1987)ን ጠቅሶ በአቀራረቡ ተማሪዎች በሚማሩበት የሚፈፅሟቸውን ተግባራት እንደሚከተለው ዘርዝሯል፡፡

- የራሳቸውን የህይወት መንገድ ይፈልጋሉ.
- ስለ ቋንቋ አጠቃቀም መረጃ ያደራጃሉ.
- ትጉህ ሰራተኛ ይሆናሉ.
- ትምህርቱ ላይ ያላቸውን እርግጠኛ ያለመሆን ችግሮች ያስወግዳሉ.
- ለማስታወስ የሚረዳ ዘዴን ይጠቀማሉ.
- ስህተት አልባ ስራን ማከናወን ይጥራሉ.
- የስነ-ልሳን ችሎታቸውን ይጠቀማሉ.
- ከይዘቱ መረዳትን ይፈቅዳሉ.
- የተለያዩ የመናገርና የመፃፍ ብልሃቶችን መጠቀም ይችላሉ.
- ምክንያታዊነትን ስራ ላይ ያውላሉ.
- ግለሰባዊ ልዩነትን ይጠቀማሉ፤ ይረዳሉ.
- የትምህርቱ ግብና አላማ ለተማሪዎች የተተው መሆኑን አውቀው ይሰራሉ.
- የመማር ማስተማሩ ንሺ በራሳቸው ይፈጥራሉ.
- እንዴት መማር እንዳለባቸው ይማራሉ.

ምሁራኑ በተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች የሚኖራቸውን ሚና በዝርዝር ገልጸዋል፡፡ የተዘረዘሩት ሚናዎች ተማሪዎች በተለይ በቋንቋ ትምህርት የሚኖራቸውን ድርሻ የሚያመለክት ነው፡፡

### 2.2.2. በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የመምህሩ ሚና

በተማሪ-ተኮር አቀራረብ መምህራን በርካታ ተግባራትን የሚፈፅሙ ባለሙያዎች ናቸው፡፡ በአቀራረቡ መምህራን የሚኖራቸውን ሚና አስመልክተው (Mc-Combs and

Whisler 1997) በተማሪ-ተኮር አቀራረብ መምህራን የትምህርት ይዘታቸውን የሚያውቁ፤ ከሁለም ተማሪዎች ጋር በጋራ የሚሰሩ ፣ እንደ አሳዳጊዎች ሀላፊነት የሚሰማቸው ፣ ተማሪዋቻቸውን የሚያከብሩ ፣ በተማሪዎቻቸው ፍላጎት የሚረኩ ፣ በሙያዊ ዕድገታቸው ተሳታፊ የሆኑ፣ በራሳቸው የሚተማመኑና እውቀት አንፀባራቂዎች፣ ለተማሪዎቻቸው ጥሩ የመማር አውድን የሚያመቻቹ፣ የትምህርቱን ሂደት ከተማሪዎች ችሎታ ጋር የሚያስማሙ ፣ የተለያዩ ፅንሰ ሀሳቦችን የሚያገናኙ ፣ ግትር የማስተማር ልምድ የሌላቸው፣ የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅመው የሚያስተምሩ፣ መልካም የክፍል ቁጥጥር የሚያደርጉና የራሳቸውን ድክመት የሚቀበሉ ናቸው።

በአቀራረቡ የክፍል ውስጥ ሂደት አብዛኞዎች ስራዎች የሚከናወኑት በተማሪዎች ነው። መምህሩ በዚህ ሂደት በአብዛኛው ተማሪዎችን የማበረታታት፣ ማማከርና የማነሳሳት ተግባራት ያከናውናል። በክፍል ውስጥ ለሚያከናውኗቸው ተግባራት ተማሪዎችን የተለያዩ ብልሃቶችን በመጠቀም ያነሳሳል። በስራቸው ሂደት ለሚገጥማቸው ችግሮች የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በመጠቆም ፣ በቡድን ውስጥ በመሳተፍ ያማክራቸዋል። እንደ (Oskarsson 1978) መምህሩ በአማካሪነት ተግባሩ የተማሪዎችን ፍላጎት የመረጃ ምንጭነት በትክክል መጠቀምና መቆጣጠር መቻሉ ምንና እንዴት ማስተማር እንዳለበት የሚያግዘ ጉልበት ከመስጠቱም በላይ በትክክለኛ ውሳኔ እንዲወስን ያስችለዋል። ይህን ሀሳብ በማጠናከር ሙሉጌታ (1996:37) ከዚህ በተጨማሪ የቋንቋውን ትምህርት በተማሪዎች ዙሪያ ማቀናጀት፣ ማስማማት፣ የተማሪዎችን ፍላጎት መረዳትና የሚያስፈልጋቸውን የመረጃ ምንጭ ብዛት ተግባር ላይ ለማዋል ያግዘዋል። ከዚህም ሌላ ተማሪዎች ምን ይፈልጋሉ? ምንስ ያደርጋሉ ችሎታቸውስ ምን ያህል ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመለስስ፣ ተማሪዎችን በፍላጐታቸው ለመለየት፣ ለመመደብ የመረጃ ምንጭነታቸውን በተገቢው መንገድ ለመጠቀምና ለማዳበር ፣ የተማሪዎችን የትምህርት አካሄድ ለመከተልና ተሳትፎዎቻቸውን በማጠናከር በትምህርቱ ዙሪያ ጠቃሚ የሆኑ አስተያየቶችን ለመስጠት እንዲችሉ ያግዘዋል" በማለት መምህሩ በአቀራረቡ የሚኖረውን ሚና ጠቁሟል።

መምህሩ ትምህርቱን መምራትና የመማሪያ ክፍሉን በብቃት ማስተዳደር ይጠበቅበታል። ይህን ለማሳካት ደግሞ (Reed and Bergmann 1995) የሚከተሉትን ነጥቦች ጠቅሰዋል፡

- ትክክለኛና የማያሻማ ትዕዛዝ ይሰጣል።

- ልምምዶችንና መልካቸውን ይወስናል።የመማሪያ አካባቢውን በመወሰን ተማሪዎች የትምህርቱን ግብ እንዲጨብጡ ያደርጋቸዋል፡፡

- ትብብራዊ መማርና ችግር በመፍታት ረገድ በቡድን ሆነው በቋንቋው እንዲገለገሉ ያነቃቃል፣ ያደፋፍራል።

- በክፍል ውስጥ የሚሰሩ ልምምዶች መረጃን መለዋወጥ የማያስችሉ ለመተጋገዝ ምክንያት የሚፈጥሩ የአመለካከት መጋራት የሚያመጡ መሆናቸውን በመፈተሽ አገልግሎታቸውን ያረጋግጣል፣ ይገመግማል፡፡

የሚሉ ናቸው፡

## 2.3. የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ዘዴዎች

በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ ትምህርቱን ንቀት በተላበሰ መንገድ ለመስጠት እጅግ በርካታ ዘዴዎች አሉ፡፡ (Leu 1998:5) እንደገለፁት እንዲሁም ከድህረ-ገጽ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ንቁ ተሳታፊ የሚያደርጉ ብለው የሚከተሉትን ዘዴዎች ዘርዝረዋል፡፡ እነዚህ ዘዴዎች በአባሪ ሀ ውስጥ ተካትተዋል፡፡

በሌላ በኩል (Moore 2001:32) በበኩላቸው በዚህ አቀራረብ ውስጥ የሚካተቱና ተማሪዎችን ንቁ ተሳታፊ የሚያደርጉ እጅግ በርካታ ዘዴዎች እንዳሉ ገልጸዋል፡፡ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የማስተማሪያ ዘዴዎች ከፍ ሲል በምሁራኑ እንደተገለፀው እጅግ በርካታ ቢሆኑም የተለመዱና አብዛኛውን ጊዜ ከሚያገለግሉ የሚከተሉትን ዘዴዎች ለናሙና በዝርዝር እንመለከታለን፡፡ እነዚህም ግኝታዊ ዘዴ፣ የቡድን ውይይት፣ የፕሮጀክት ስራ ፣ ትብብራዊ ትምህርት ፣ የሚና ጨዋታ ፣ ችግር ፈቺ ዘዴ የብጤ ማስተማር ወዘተ ያሉ ናቸው፡፡

### 2.3.1. ግኝታዊ የማስተማሪያ ዘዴ (Discovery Learnig)

እንደ እነ Moore (2001:134) ፣ Callahan (1988) ፣Borich (1988) አገላለፅ ግኝታዊ ዘዴ ተማሪው በችግር ፈቺ ተግበራት ላይ በመሳተፍ እውቀቱን ወይም ክሂሉን የሚያሳድግበት መንገድ ነው ይላሉ፡፡ ግኝታዊ ዘዴ፣ ተማሪዎች በነበራቸው ነገር ታግዘው አዳዲስ ነገሮችን የሚያገኙበት ነው፡፡ ተማሪዎች የራሳቸውን አእምሮታዊ ችሎታ በመጠቀም አዳዲስ ነገሮችን ሊማሩ የሚችሉበት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

ግኝታዊ ዘዴ ሁለት ትምህርታዊ ፋይዳዎች እንዳሉት (ICDR 1999) ላይ ተገልጿል፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ተማሪዎች በራሳቸው መነሳሳት ነፃ ሆነው የማሰብ ዕውቀት የመገብየት ዕድል ይሰጣል፡፡
- ተማሪዎች ዕውቀት የሚገበዩበትን መንገድ እንዲያውቁ ያግዛል። ይህ በራሳቸው ግንዛቤ መረጃ በመሰብሰብ፣ በማንቀሳቀስና በማደራጀት ዕውቀት ማግኘትን ለማሳየት ነው፡፡

በሌላ በኩል ግኝታዊ ዘዴ ቀጥሎ የተጠቀሱ ጠቀሜታዎች እንዳሉት (ICDR 1999) እና (Cruickshank እና ሌሎች 1999 ፡ 183) ገልጸዋል፡፡

- ትምህርቱ የበለጠ ትርጉም እንዲኖረው በተማሪዎች አእምሮ እንዲቀር እና አዲስ እንዲሆን ይረዳል፡፡
- መነሳሳትን (Motivation) ፍላጎትና እርካታን ይጨምራል፡፡
- እውቀታቸው እንዲያድግ መረጃዎች በመስጠትና ችግር ፈቺ ክህሎትን እንዲያጐለብቱ ያደርጋል፡፡
- ተማሪዎች በአዲስ አውድ ውስጥ ችግር እንዲፈቱ ያግዛቸዋል ይህ ደግሞ መማርን ያፋጥናል፡፡
- ለተማሪዎች ነፃነትን ያጐናፅፍል
- የተፈጥሮ ችሎታቸውን በዕወቀት ላይ እንዲያውሉ ያግዛል፡፡
- በእርስ በርስ ግንኙት ጊዜ አዎንታዊ አመለካከትን እንዲፈጥሩ ያደርጋል፡፡ ይላሉ፡፡

### 2.3.2. የፕሮጀክት ዘዴ (Project Method)

እንደአብዱራህማን (1983፣50) ገለጻ ፕሮጀክት ዘዴ የአንድ ክፍል ወይም የአንድ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የአካባቢያቸውን ሁኔታ በህብረት ሆነው የሚያጠኑበት ነው፡፡ ጥናቱ የሚካሄደው በመምህሩ መሪነትና በተማሪዎቹ ተሳታፊነት ይሆናል፡፡ በመቀጠልም የማስተማሩን ሂደት እንዴት ማደራጀት እንደሚችልና፣ በዚህ ዘዴ ተጠቅሞ ማስተማር የሚሰጠውን ጥቅም እንደሚከተለው አብራርተዋል፡፡

ለፕሮጀክት ስራ መምህሩ የአንድን ክፍል ወይም የትምህርት ቤቱን ተማሪዎች በቅድሚያ ያደራጃል፡፡ በመጀመሪያ መምህሩ ተማሪዎች በትንንሽ ቡድኖች ይከፋፈላል፡፡ ጥናት ርዕሶችን እንደየተማሪዎቹ እድሜና ፍላጎት ለያይቶ ለየቡድኖቹ ያድላል፡፡ የሚሰጡት ፕሮጀክቶች በአጭር ወይም በረጅም ጊዜ/ ከ3-5 ሳምንት/ ተሰርተው የሚያበቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

መምህሩ የፕሮጀክቱ ስራ እንዴት መከናወን እንዳለበትና የፕሮጀክቱ ዓላማ ግቡን እንዲመታ ምን መደረግ እንዳለበት በተማሪዎቹ እየተረዳ ስራውን በሚገባ ማቀድ ይኖርበታል። የፕሮጀክቱም ዓላማ በቀላሉ ተማሪዎች ሊረዱት የሚችል መሆን ይገባዋል። በፕሮጀክቱ ስራ ላይ የሚሳተፉ ተማሪዎች ስራውን ከመጀመራቸው በፊት ከዕቅዱ ጋር በሚገባ መተዋወቅ ይኖርባቸዋል። ፕሮጀክቱም የተማሪዎቹን የመመራመርና አዳዲስ ነገሮችን ለማወቅ የሚያስችልና የአካባቢያቸውን ችግር እንዲፈቱ የሚያደርግ መሆን አለበት።

የፕሮጀክት ስራ አያሌ ጥቅሞች አሉት፡፡ መጀመሪያ ተማሪዎች ማቀድና ተግብረው መስረትን ይለማመዳሉ፡፡ በተጨማሪም ከአካባቢያቸው ችግር ጋር ይተዋወቃሉ፡፡ በስራ ሂደቱም ውስጥ ለህብረተሰቡ የሚጠቅሙ ዕቃዎችን እንዲያመርቱና ጠቃሚ ሐሳቦችን እንዲሰነዝሩ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ በአጠቃላይ በፕሮጀክት ስራ አማካይነት ስርዓተ ትምህርትን ከተማሪዎችና ከአካባቢው ህዝብ ኑሮ ጋር ለማዛመድ መልካም አጋጣሚ ይገኛል፡፡

የፕሮጀክት ዘዴ ተፈጥሮአዊ ፣ ከህይወት ጋር ተያያዥነት ያለው የመማር ተግባር ሲሆን ተማሪዎች በግል ወይም በቡድን ሆነው ችግሮችን የሚመረምሩበትና መፍትሄ የመያገኙበት ነው (ICDR 1999:84)። በአጠቃላይ ይህ ዘዴ ከእውናዊ የህይወት

ክስተቶች ጋር የጠበቀ ግንኙነትን የሚፈጥር ፣ በተማሪዎች መካከል ያለውን የትብብር መንፈስ የሚያጠናክር ነው።

### 2.3.3. ትብብራዊ ትምህርት (Cooperative Learnig)

እንደ (Richards and Rodgers 2001:192) በትብብራዊ የትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች በአብዛኛው በጥንዶችና በትንንሽ ቡድኖች ሆነው ስለሚሰሩ ተማሪዎች በአብዛኛው የመተባበር ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡ ትብብራዊ ትምህርት በቡድን የመማር ተግባር ላይ የተመሠረተ በመሆኑ መማርን በማህበራዊ የመረጃ ልውውጥ ላይ እንዲያተኩር አድርጎታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በቡድኑ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች በትምህርታቸው ሀላፊነት እንዲሰማቸውና ሌሎች እንዲማሩ ለማድረግ እንዲነሳሱ ያደርጋቸዋል፡፡ ትብብር (Cooperation) ግለሰቦች በቡድን ውስጥ ራሳቸውን የሚጠቅሙ ውጤቶች (outcomes) ከማግኘታቸው ባሻገር ለሌሎችንም የቡድኑ አባላት ይጠቅማሉ፡፡ ትብብራዊ ትምህርት በአብዛኛው አራት አባላት ባሏቸው ትንንሽ ቡድኖች ይከናወናል፡፡ በመሆኑም በቡድኑ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች እርስ በርስ የጠበቀ ትስስር ስለሚኖራቸው የራሳቸውንና የሌሎችን መማር ያሳድጋሉ በማለት ምሁራኑ አብራርተዋል፡፡

በትብብራዊ የትምህርት ሂደት በተማሪዎች መካከል አዎንታዊ መደጋገፍ ይከሰታል፡፡ በዚህ መሠረት አንድ ተማሪ የትምህርቱን ግብ በተመሳሳይ ሲያሣካ ሌሎችም ተማሪዎች ያሳካሉ፡፡ በማለት እነ (Johnson and Johnson 1989) ስለትብብራዊ ትምህርት ጠቀሜታ ገልፀዋል፡፡

#### 2.3.3.1. የትብብራዊ ትምህርት መርሆዎች

በትብብራዊ ትምህርት በርካታ መርሆች ተቀርፀዋል፡፡ ነገር ግን ከድህረ ገፅ (http://www.Secondaryschools.com/approach.html.) የተገኘው መረጃ የሚከተሉት ስምንቱን ዋና ዋናዎቹ በማለት ዘርዝሮዋቸዋል፡፡

- የስብጥር ቡደና (**Heterogenous grouping**) ፡- በዚህ መርህ መሠረት በትብብራዊ ትምህርት ወቅት የሚቀናጁ የቡድን አባላት የተለያዩ መሆን አለባቸው፡፡ ይህም ማለት የቡድኑ አባላት በፆታ፣ በዘር፣ በማህበራዊ መደብ፣

በሀይማኖት፣ በስብዕና፣ በዕድሜ፣ በቋንቋ ችሎት ልዩነታቸው ተቀላቅለው ቡድን መመስረት መቻል አለባቸው፡፡

- **የተቀናጁ ክሂሎች (Collaborating Skills)** በጋራ ለመስራት የሚያስችሉ ክሂሎች ናቸው፡፡ተማሪዎች በጋራ መስራት እንዲችሉ የሚያግዙ ክሂሎች ናቸው፡፡

- **ቡድናዊ ጥንካሬ (Group autonomy)** ይህም መርህ ተማሪዎች የተለያዩ ግብአቶችን ለማግኘት መምህሩን ከመጠየቅ በተጨማሪ ወደ ራሳቸው እንዲያዩ ያበረታታቸዋል፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲገጥሟቸው ለመምህሩ መናገርና መረዳት እዲሁም ራሳቸውን መረዳት መቻል አለባቸው፡፡

- **በተመሣሣይ ጊዜ መሳተፍ (Simultanous interaction)** በአንድ ክፍል ውስጥ የቡድን ስራ ከሌለ መደበኛ ንግግር ብቻ ይከናወናል፡፡ ይህም ቅደም ተከተላዊ አካሄድ ያለው በመሆኑ በክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የመናገር እድል የሚያገኙት አንዱ ተናግሮ ሲጨርስ ነው፡፡ ነገር ግን በክፍል ውስጥ የተለያዩ ቡድኖች ተደራጅተው ከሆነ በተመሳሳይ ጊዜ ቡድኑ ውስጥ ብዙ ተማሪዎች የመናገር እድል ያገኛሉ፡፡

- **እኩል ተሳትፎ (Equal participation)** የቡድኑ ስራ ችግር ከቡድኑ አባላት ውስጥ አንዱ ወይም ሁለቱ አባላት የበላይ ስለሚሆኑ የሌሎች ተሳትፎ ይገታል፡፡ ትብብራዊ ትምህርት በቡድን ውስጥ የአባለት እኩል ተሳትፎ እንዲኖር ያበረታታል፡፡

- **ግለሰባዊ ተጠያቂነት (Individual accountability)** በቡድን ውሰጥ ግለሰባዊ ተጠያቂነትን ስንፈጥር እያንዳንዱ የቡድን አባል (ተማሪ) ከሌሎች የቡድኑ አባላት ሊማር እንደሚችልና እውቀቱን ለሌሎች ማካፈል እንደሚችል እናሳስባለን፡፡

- **አዎንታዊ መደጋገፍ (Positive interdependent)** ሲከሰት አንዱ አባል ለሌሎች አባላት ምን እንደሚጠቅምና ምን እንደሚጎዳ ያስባሉ፡፡ ይህም ሁሉ ለአንዱ አንዱ ለሁሉ (all for one, one for all) የሚለውን ሃሳብ የያዘ ነው፡፡

- ለመተባበር ዋጋ መስጠት (Cooperation as a value) በዚህ መርህ መሠረት ትብብራዊ የመማሪያ ዘዴ ብቻ ላይሆን ይችላል፡፡ ከማስተማሪያ መንገድነት ወይም እንዴትነቱ ባሻገር የይዘትም ክፍል ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ሊመጣ የሚችለው በጣም ጠቃሚ ከሆነው የአዎንታዊ መደጋገፍ አስተሳሰብ ነው፡፡ በመሆኑም ለትብብር ዋጋ መስጠት "ሁሉ ለአንዱ፣ አንዱ ለሁኑ የሚለው" ሀሳብ የሚያጠናክር ነው።

### 2.3.4. የጥያቄ አቀራረብ ዘዴ (Questioning method)

በክፍል ውስጥ ተማሪዎች በሚማሩበት ጊዜ አንድ መምህር ተማሪዎቹን ስለሚማሩት ነገር ጥያቄ ይጠይቃል፡፡ ጥያቄ መጠየቅ ከማስተማር ሂደቶች አንዱ በመሆኑ መምህሩ ጥያቄ የሚያቀርበው ያስተማረውን ትምህርት ተማሪዎቹ በሚገባ መከታተል አለመቻላቸውን ለማወቅ ነው። ለጥያቄው ትክክለኛውን መልስ ካገኘ ማስተማሩን ይቀጥላል፡፡ የተሰጠው መልስ መምህሩን ካላረካው ግን ትምህርቱን በመድገምም ሆነ ዘዴውን በመቀየር ተማሪዎቹ የተሻለ ግንዛቤ እንዲያገኙ ለማድረግ ይሞክራል፡፡

### 2.3.5. የቡድን ስራ (Group Work)

ተማሪዎችን በቡድን መድቦ ማወያየት ከማስተማር ዘዴዎች አንዱ ነው፡፡ በዚህ አሰራር ስልት መምህሩ የክፍሉን ተማሪዎች በትንንሽ ቡድኖች ይመድባል። ተማሪዎቹ ትምህርታቸውን በቡድን ሆነው እንዲከልሱና ግልጽ ያልሆነውን እርስ በርሳቸው እንዲወያዩበት ያደርጋል፡፡ አሰራሩ የተማሪዎቹን ስራና ችሎታ በቅርብ ለመከታተል መምህሩ የሚያስችለው ይሆናል፡፡ መምህሩ የቡድን አባልና የቅርብ ረዳት ነው፡፡

በክፍል ውስጥ መምህራን የቡድን ስራን እንዲያከናወኑ የሚያደርጓቸው ምክንያቶች አሉ። ይህንን አስመልክቶ አብዱራህማን (1983 :48) የቡድን ውይይት በስራ ላይ የሚውልባቸው ሁኔታዎች እንደሚከተለው ጠቅሰዋቸዋል።

- መምህሩ አዲሱን ትምህርት ካስተዋወቀ በኋላ ተማሪዎች ስለተዋወቁት ትምህርት ምን እንደሚያውቁ ለመረዳት ተማሪዎቹን በቡድን እንዲወያዩ

ያደርጋቸዋል፡፡ እዚህ ላይ ተማሪዎቹ ሐሳባቸውን በትምህርቱና ትምህርቱ በሚሰጠው ጥቅም ላይ እንዲያተኩሩ ይጠየቃሉ፡፡

- ሁለተኛው የመወያያ ሁኔታ ቀደም ሲል ከመምህሩ የቀረበውን ትምህርት እንዴት በስራ ላይ ለመተርጉም እንደሚቻል ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች የተማሩትን እውነታ እንዴት በስራ ላይ በጋራ ለማዋል እንደሚችሉ ለመረዳትና እገዛ ለማድረግ ይሆናል፡፡

2.3.5.1. የቡድን አመዳደብ አይነቶች (**Kinds of grouping**)

እንደ አብዱራህማን (1983:49) የሚከተሉት የቡድን አይነቶች መምህራን በክፍል ውስጥ በአብዛኛው የሚጠቀሟቸው ናቸው፡፡

ሀ. የእቅድ አልባ የቡድን አመዳደብ (**Arbitrary Grouping**)

እቅድ አልባ የቡድን አመዳደብ የሚባለው መምህራን የክፍላቸውን ተማሪዎች እንደ አቀማመጣቸው ከዚህ በመለስ በአንድ ቡድን ሁኑ በማለት ወይም በተማሪዎች ስም ተራ መሰረት እነሱን በተለያዩ ቡድኖች በመመደብ ውይይት እንዲያካሂዱ ያደርጋሉ፡፡

ለ. በችሎታ ቡድን መመደብ (**Ability grouping**)

በችሎታ በቡድን አመዳደብ ዘዴ መምህራን የክፍሎታቸውን ተማሪዎች እንደየችሎቸው ማለት ተመሳሳይ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች በአንድ ቡድን በማድረግ እንዲወያዩ ያደርጓቸዋል፡፡በእንደዚህ ያለ አሰራር መምህሩ ለአንድ ትምህርት ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውን እንደየችሎታቸው በተለያዩ ቡድኖች በማድረግ በየቡድናቸው እንዲወያዩ ያደርጋሉ፡፡ ከፍ ያለ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች የተሰጣቸውን ርእስ ተወያይተው በመጨረስ ወደ ሌላ ሲሸጋገሩ አዝጋሚዎቹ ግን ስራቸውን ለማገባደድ የመምህሩን እርዳታ ይሻሉ ሆኖም እንደዚህ ያለ አመዳደብ ጥንቃቄን የሚጠይቅና አንዳንዴም ዝቅተኛ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች የዝቅተኛነት መንፈስ እንዲሰማቸው የሚያደርግ ስለሆነ በብዙ መምህራን ዘንድ እምብዛም አይወደድም፡፡

### ሐ.የተለያዩ ችሎታ ቡድን አመዳደብ (Mixed abiity grouping)

የተለያየ ችሎታ ቡድን አመዳደብ በውስጡ ከፍተኛ፣ መካከለኛ ዝቅኛ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ያሉበት ነው፡፡ በዚህ ቡድን ውስጥ ጎበዝ ተማሪ ደከም ያሉትን ይረዳል፡፡ በአንፃሩ ደካሞች ከጎበዞቹ በሚሰጣቸው እርዳታ ችሎታቸውን ያሻሽላሉ፡፡ በተጨማሪም የሚሰጣቸውን ስራ ተማሪዎቹ እንደችሎታቸው ይከፋፍሉታል፡፡ በዚህ ረገድ ለጎበዞቹ ከበድ ያለ ስራ ሲሰጣቸው ደከም ለሚሉ ግን ቀለል ያለው ይሰጣቸዋል፡፡ ሁሉም በስራቸው በመርካት ይሰራሉ፡፡ በስራውም ሂደት ውስጥ ሁሉም ትምህርት ያገኙበታል፡፡

### መ. የአቻ ቡድን አመዳደብ (Compatibility grouping)

የመቀራረብ ቡድን አመዳደብ የሚያመለክተው እርስ በርስ የሚስማሙና በአንድ ላይ ለመስራትየሚፈልጉ ተማሪዎችን መምህሩ በየቡድኑ መመደብ እንዲማማሩ የሚያደርግበት የአሰራር ስልት ነው፡፡ ተማሪዎች ቡድኖቻቸውን ለመመስረት ተጠቋቁመው ይመራረጣሉ፡፡ በመሀሉ ግን ጥቂት ተማሪዎች ማንም ሳይመርጣቸው ያለ ቡድን ሊቀሩ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ግን መምህሩ ቡድኖችን በማግባባት እንደዚህ ያሉ ተማሪዎች በየቡድኖቹ እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡

### 2.3.6. የሚና ነጠቃ ዘዴ (Role Playing Method)

ሚና መጫወት የሚለው ቃል እንደሚያመለክተው ተማሪዎች በኑሮ ላይ ስለሚገጥሟቸው ሰዎች ወይም እንስሳት በማስመሰል ለሌሎች በትርኢት መልክ የሚያሳዩበት አሰራር ነው፡፡ በዚህ አይነት አሰራር መጠቀም የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ስለ ሌሎች ሰዎች/ እንስሳት/ ስሜትና ጠባይ አውቀው በሚያገኙት ትምህርት ጠባያቸውንና አሠራራቸውን እንዲያሻሽሉ ለማድረግ ነው፡፡

ተማሪዎች የሚጫወቱትን ሚና በሚገባ እንዲወጡና ትምህርትም እንዲቀስሙበት መምህሩ አስፈላጊውን ዝግጅት ያደርጋል፡፡ መምህሩ ያዘጋጀውን የድርጊት ፕሮግራም ለእያንዳንዱ የተማሪ ተዋናይ ሚናውን በመስጠት ይህንኑ እንዲጫወት ያደርጋል፡፡

### 2.3.7. ችግር ፈቺ ዘዴ (Problem solving methods)

በችግር ፈች ዘዴ ተጠቅሞ ማስተማር ዋና ጥቅሙ የህብረተሰቡን ችግሮች ለማቃለል ምሁራን የሚጠቀሙበትን የአሰራር ዘዴ ተማሪዎች እንዲያውቁና በመጠኑም ቢሆን እነርሱም እንዲጠቀሙበት ለመረዳት ነው፡፡

## 2.4. የአሳታፊ ትምህርት ትግበራን የሚያደናቅፉ ችግሮች

የተለያዩ ምሁራን እንደሚገልጹት የአሳታፊ ትምህርት ትግበራን ውጤታማ እንዳይሆን የሚደርጉ በርካታ እንቅፋቶች አሉ። ከእነዚህ ጥቂቶቹ ቀጥሎ ይቀርባሉ።

(Cruikshank እና ሌሎች 1999) የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ችግሮችን በአራት ዋና ዋና ክፍሎች አጠቃልለው መድበዋል።

እነርሱም፡-
1. ከግለሰብ ባህሪያት ጋር የተያያዙ ምክንያቶች
2. ከትምህርት ልምዶች ጋር የተያያዙ ምክንያቶች
3. የሰብዕና ተጽዕኖ ምክንያቶች
4. ከተለያዩ አውዶች ጋር የተያያዙ ምክንየቶች ናቸው።

በሌላ መልኩ እነ O'HARA and O'HARA (1998) ፣ Leu (2000) ፣ Squazzin Graan (1998) አቀራረቡን ሊያደናቅፉ የሚችሉትን እንቅፋቶች እንደሚከተለው አይተዋል።

### 2.4.1. መምህራንና ተማሪዎች በተማሪ-ተኮር ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት

በአሳታፊ የትምህርት አቀራረብ የመምህራኑና የተማሪቹ አመለካከት ቀደም ሲል ካላቸው ግንዛቤ ወይም ዕውቀት ጋር እጅግ የተጠበቀ ነው። ይህም ማለት ተማሪዎችና መምህራን ቀደም ሲል የነበረውን መምህሩን ብቻ የዕውቀት ምንጭና ከማንም የበለጠ አዋቂ የሚያደርገውን የጥንታዊ አቀራረብ የለመዱት በመሆኑ ስለሚደግፉት ነው። በእነዚህ ተማሪዎችና መምህራን ማስተማር በመማር ላይ የበላይነትን ሚና ይወስዳሉ። በመሆኑም ተማሪዎች በመምህሩ የሚሞሉ ባዶ ዕቃዎች ተደርገው ይታሰባሉ O'HARA

and O'HARA (1998:78)። እነዚሁ ጸሐፊዎች ጨምረው እንደገለጹት" በእነሱ አስተሳሰብ መሠረት ይህ አሳታፊ ዘዴ እንዲወገድ ይፈልጋሉ።"

### 2.4.2. የመማሪያ ክፍል ሁኔታ /classroom condition/

ለአንድ ተቋም ከማህበራዊ አካባቢው ባሻገር የሚገኝበት ቦታ ፣ ስፋቱ ፣ ያለው ቅርፅና የመማሪያ ክፍሎቹ ግንባታ ፣ የተለያዩ እንደ ቁሳቀስ ፣ የንብረት ማዕከል ፣ የቤተ ሙከራና የቤተመፃህፍት ያሉ የማስተማሪያ አገልግሎቶች መኖርና በአግባቡ መተዳደር ፣ ወዘተ ከማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የላቸው ናቸው።

(Leu 2000፡17) እንደገለጹት ብዙ ተማሪዎችን በተጨናነቀ ክፍል ውስጥ የሚያስተምሩ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የተለያዩ ስራዎን ለመስጠትና በቡድን ለማሰራት ምቾት አይሰማቸውም። መምህራን በተጨናነቁ የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ተግባራዊ ስራዎችን ፣ ችግር ፈቺ ዘዴዎችን ማከናወን ይቸገራሉ።

### 2.4.3. የተማሪዎች ብዛት /Class size/

በብዙ ተማሪዎች ከመጠን በላይ የተጨናነቀ የመማሪያ ክፍል የተለያዩ የሙከራ ስራዎችን ለማሰራትና የቡድን ስራዎችን ለማሰራት አይመችም። (Squazzin and Graan 1998፡54) በጥናታቸው እንዳመለከቱት በብዙ የአፍሪካ ክፍሎች የሚገኙ ትምርት ቤቶች በርካታ ቁጥር ባላቸው ተማሪዎች የተጨናነቁ ናቸው። በመሆኑም ለተማሪዎች በቂ ትኩረት ለመስጠትና የእያንዳንዱን ተማሪ ፍላጎት በማወቅ በትምህርቱ ሂደት በንቃት ለማሳተፍ አስቸጋሪ ይሆናል።

### 2.4.4. አካላዊ አካባቢ /Physical environment/

በብዙ ትምህርት ቤቶች እንደተረጋገጠው አካላዊ አካባቢ ክፍሎች አደራደር ፣ የቁሳቁስ አደራደር ፣ የመማሪያ ክፍል ገጽታ ወዘተ...) አሳተፊ ዘዴን ለመተግበር አስተዋጽኦ ያደርጋል። ንፁህና በጥሩ ሁኔታ የተጠበቀ ተስማሚ እንዲሁም ንፁህ አየር ያለው የመማሪያ ክፍል አሳታፊ ትምህርትን ለመተግበር አወንታዊ አስተዋጽዖ አለው (Squazzin and Graan 1998፡77)።

### 2.4.5. በመማሪያ መፅሀፎችና በሞጁሎች ላይ ያለመካተት

አብዛኛዎቹ የመማሪያ መፃህፍትና ሞጁሎች ተማሪ-ተኮር አቀራረብ ዘዴን ታሳቢ አድረገው አይዘጋጁም። ለአንድ መንገድ ትምህርት ብቻ የሚያገለግሉ ናቸው። በአንድ መንገድ ተግባቦት ተማሪውን የተፃፈውን ነገር ብቻ እንዲያነብ እንጂ ለሚነበበው ነገር የተብራራ መልስ የሚሰጥበት መንገድ የለም። ይህም ተማሪዎችን በአብዛኛው ከውስጣቸው ሀሳብ አመንጭተው እየገለጹ የሚማሩበትን እድል አይፈጥርም (Leu 2000:86)::

## 2.5. የቀደምት ስራዎች ቅኝት

በዚህ ክፍል የቀረቡት ጉዳያቸው ከዚህ ስራ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ቀደምት ስራዎች ናቸው። የተተኮረባቸው ነጥቦችም በጥናቱ ርዕስ ፣ በአላማ ፣ በአጠናን ዘዴና በግኝት ዝምድና ላይ ያተኮሩ ናቸው።

ሙሉጌታ ይታየው 1996 "የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኮመትኮ ሴርቲፍኬት መርሃግብር እንደታየው" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዷል፡፡ የጥናቱም አላማ በኮመትኮ የሰርፍኬት መርሃግብር ያለውን የተማሪ ተኮር አቀራረብ የአተገባበር ሁኔታ መፈተሽ ላይ የሚያተኩር ነው። ጥናቱን ለማካሄድ የተጠቀመበት የአጠናን ዘዴ ተተኳሪዎችን ለመምረጥ የታቀደ የንሞና ዘዴ የተጠቀመ ሲሆን መረጃ ለመሰብሰብ የክፍል ውስጥ ምልከታ ፣ ቪዲዮ ቀረፃ ፣ የተማሪዎች የዕለት ሁኔታ ማስታወሻ ፣ የፅሑፍና የቃል መጠይቅ ተጠቅሟል። የጥናቱ ግኝትም ተማሪ-ተኮር አቀራረብ በኮሌጁ የሰርቲፍኬት መርሃግብር በአማርኛ ኮርሶች ሲተገበር የታየ ቢሆንም በቡድን የአባላት ብዛት፣ ሁሉም የቡድኑ አባላት በጋራ ስራዎች ላይ እኩል ተሳትፎ አለማድረግ፣ የጊዜ እጥረት የሚሉ ችግሮች አቀራረቡን በመተግበር ሂደት የሚገጥሙ ሆነው ተገኝተዋል።

ኤልያስ አድማሱ 1997 የጥናቱ ርዕስ "በኦሮሚያ መምህራን ትምህርት ኮሌጆች ውስጥ መሠረታዊ አማርኛን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ" የሚል ሲሆን የጥናቱ አላማ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በሚገኙ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች በመሠረታዊ አማርኛ ኮርሶች አሰጣጥ ወቅት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበርን መፈተሽ ነው። ጥናቱን ለማካሄድ የአጠናን ዘዴ የክፍል

ውስጥ ምልካታ ፣ የቪዲዮ ቀረፃ ፣ ፎቶግራፍ፣ ቃለ መጠይቅ፣ የፅሁፍ መጠይቅና የሰነድ ፍተሻ ናቸው። በግኝቱም በክልሉ በሚገኙ የመምህራን ኮሌጆች አቀራረቡ በመሠረታዊ አማርኛ ኮርሶች ተዘውትሮ እንደሚተገበር አረጋግጧል።

ደረጀ ነጋሽ 1999 "የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር ፍተሻ በደብረማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የአማርኛ ትምህርት ክፍል በ10+3 የስልጠና መርሃግብር" በሚል ርዕስ ጥናቱን አካሂዷል፡፡ የጥናቱ አላማም በ1999 ዓ.ም. በደማመትኮ አማርኛ ትምህርት ክፍል 10+3 የስልጠና መርሃግብር የተማሪ-ተተኮር የትምህርት አቀራረብን አተገባበር መፈተሽ ላይ ያተኮረ ነው። የአጠናን ዘዴው ተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ ፣ የቪዲዮ ቀረፃ፣ የፅሁፍ መጠይቅ፣ የቃል መጠይቅና የተማሪዎች የዕለት ውሎ ማስታወሻ በመረጃ ማሰባሰቢያነት የተጠቀማቸው መሣሪያዎች ናቸው። የጥናቱ ግኝት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር በደማመትኮ ጥሩ በሚባል ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አረጋግጧል።

ይህ ጥናት ከፍ ሲል ከተዘረዘሩት ጥናቶች ጋር ያለው ዝምድና ሲመረመር ጥናቶቹ ባነሱት ርዕሰጉዳይ ፣ በአላማና በአጠናን ዘዴ በአብዛኛው ግንኙነት ያላቸው ቢሆንም በጥናት ዘመን ፣ ቦታ ፣ በጥናት ተተኳሪዎች መጠንና አይነት ፣ በመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች ምርጫና አይነት የአጠቃቀም እንዲሁም በግኝት ልዩነት ይታይባቸዋል።

# ምዕራፍ ሦስት

# የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት በዋናነት አሀዛዊ የአጠናን ዘዴን የተከተለ ነው። በመሆኑም ለጥናቱ ደጋፊነት የተሰበሰቡት መረጃዎች በአብዛኛው በሰንጠረዥ ተተንትነዋል። ይህ የሆነበት ምክንያት የጥናቱ አጋዥ የሆኑ መረጃዎች በአብዛኛው በምልከታና በጽሑፍ-መጠይቅ አማካይነት የተሰበሰቡ በመሆናቸው ሰንጠረዥ በመጠቀም በመቶኛ ለመግለፅ አሀዛዊ የምርምር ዘዴ አመቺ ሆኖ በመገኘቱ ነው። በተጨማሪም ጥናቱ በተወሰነ መልኩ አይነታዊ የምርምር ዘዴን ተጠቅሟል። በቃለመጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች ደግሞ በገለጻ ስልት ተተንትነዋል።

## 3.1. የጥናቱ ተተኳሪዎች አመራረጥ

### 3.1.1. የትምህርት ቤት አመራረጥ

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ይህ ጥናት የተካሄደው በካፋ ዞን የሁለተኛ ደረጃ (9ኛና 10ኛ) ትምህርት ቤቶች ላይ ነው። በመሆኑም ለዚህ ጥናት በተተኳሪነት የተመረጡት ሶስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ በካፋ ዞን ከሚገኙ አስራ አንድ የመንግስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተመረጡ ናቸው፡፡ እነዚህ ሶስት ትምህርት ቤቶች የተመረጡት በተራ የእጣ ናሙና ነው፡፡ ይህ የንሞና ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት በዞኑ ለሚገኙ ሁሉም ትምህርት ቤቶች የመመረጥ እኩል እድል ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት ትምህርት ቤቶች የሚከተሉት ናቸው።

- የጊመቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- የአውራዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ቢሻው ወ/ዮሀንስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

### 3.1.2. የምድብ አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጡት ሶስቱ ትምህርት ቤቶች ባላቸው የምድብ ብዛት ተመጣጣኝ አይደሉም። የእነዚህ ትምህርት ቤቶችና ያላቸው የዘጠነኛ እና የአስረኛ ክፍል የምድብ ብዛት በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል።

ሰንጠረዥ አንድ፡- ትምህርት ቤቶቹና ያላቸው የምድብ ብዛት

| ተ.ቁ. | የትምህርት ቤቱ ስም | የምድብ ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 9ኛ ክፍል | 10ኛ ክፍል | ጠቅላላ |
| 1. | ጊምቦ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 9 | 3 | 12 |
| 2. | አውራዳ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 6 | 3 | 9 |
| 3. | ቢሻው ወ/ዮሀንስ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 12 | 8 | 20 |
| ጠቅላላ ድምር | | | | 31 |

ከፍ ሲል በሰንጠረዥ አንድ ላይ የሰፈሩትን መረጃዎች እንደሚያመለክቱት እያንዳንዱ ተተኳሪ ትምህርት ቤት ያለውን የዘጠነኛና የአሰረኛ ክፍል የምድብ ብዛት የሚያመለክት ነው። በዚህ ጥናት እነዚህ ትምህርት ቤቶች ካሏቸው የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል ምድቦች አመቺ ወይም የግኝት ንሞና በመጠቀም ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት አራት አራት ምድቦች ተመርጠዋል። ከአንዱ ትምህርት ቤት ከተመረጡት አራት ምድቦች ሁለቱ ከዘጠነኛ ክፍል ሲሆኑ ሁለቱ ደግሞ ከአስረኛ ክፍል ናቸው። ለምድብ መረጣው አመቺ ናሙና የተመረጠበት ምክንያት የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች የሚያስተምሩ በመሆናቸው በምልከታ ወቅት የክፍል ግጭት እንዳይከሰት ታስቦ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የተመረጡት ምድቦች ቀጥሎ በሰንጠረዥ ተገልጸዋል።

ሰንጠረዥ ሁለት፡- ለጥናቱ የተመረጡ ሴክሽኖች

| የትምህርት ቤቱ ስም | የተመረጡ ሴክሽኖች | | |
|---|---|---|---|
| | 9ኛ ክፍል | 10ኛ | ብዛት |
| ጊምቦ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | ‘H’ እና ‘J’ | ‘A’ እና ‘B’ | 4 |
| አውራዳ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | ‘B’ እና ‘C’ | ‘A’ እና ‘B’ | 4 |
| ቢሻው ወ/ዮሀንስ 2ኛ ደረጃ ትምህርት | ‘C’ እና ‘J’ | ‘C’ እና ‘F’ | 4 |

### 3.1.3. መምህራን

በዚህ ጥናት የተሳተፉት መምህራን የአማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ ብቻ ሲሆኑ ጥናቱ በተከካሄደበት የትምህርት ዘመን ማለትም በ2003 ዓ.ም. በሶስቱም ትምህርት ቤቶች በተመረጡት የክፍል ደረጃዎች የሚያስተምሩ መምህራን በቁጥራቸው ሁለት ሁለት ብቻ ነበሩ። በመሆኑም በአጠቃላይ ስድስት መምህራን የዚህ ጥናት ተተኳሪ ሆነዋል። የመምህራኑ አጠቃላይ መረጃ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል።

ሰንጠረዥ ሶስት፦ የተተኳሪ መምህራን አጠቃላይ መረጃ

| ያሉበት ትምህርት ቤት | ጾታ | | ዕድሜ | | የትም. ደረጃ | | የአገልግሎት ዘመን | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | 25-35 | 35-45 | ቢ.ኤ | ኤም. ኤ | 1-10 | 11-20 | 21-35 |
| ጊምቦ | | 2` | 2 | - | 2 | - | 1 | 1 | - |
| አውራዳ | 2 | | 2 | | 2 | - | 2 | - | - |
| ቢሻው ወ/ዮሀንስ | 1 | 1 | 1 | 1 | 2 | - | 1 | - | 1 |

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

የዚህ ጥናት አብይ ትኩረት በካፋ ዞን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለጊዜ ያለውን የተማሪ-ተኮር የማስተማር ዘዴ አተገባበር መፈተሽ ነው። በመሆኑም ከጥናቱ ርዕስ ጋር ሊጣጣሙ የሚችሉ የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች ተመርጠዋል። የመረጃ መሣሪያዎቹ ከርዕሱ ጋር የሚኖራቸው ተጣጥሞ በችግሩ ዙሪያ ተጨባጭ እና እውናዊ መረጃ ለማግኘት ጠቃሚ በመሆኑ ድርሻው ላቅ ያለ ነው። በመሆኑም ይህ ጥናት የክፍል ውስጥ ተማሪ-ተኮር የማስተማር ዘዴን የክፍል ውስጥ ትግበራን የሚፈትሽ በመሆኑ አጥኚው በዋናነት የክፍል ውስጥ ምልከታን ፣ የፅሁፍ መጠይቅና ቃለመጠይቅ በመረጃ ማሳባሰቢያነት ተጠቅሟል።

### 3.2.1. የክፍል ውስጥ ምልከታ

ያለው 1998፣ 2001፡183 እንደገለጹት ምልከታ ተመራማሪው ተጠኚዎቹ እያወቁም ሆነ ሳያውቁ በሚገኙበት ቦታ በመሆን በዚያ ወቅት ምን እንደሚሰሩ፣ እንዴት እንደሚሰሩ፣ እርስ በርሳቸው እንዴት እንደሚራከቡ፣ ምን እንደሚናገሩ ወዘተ. ራሱ በሚመቸው፣ አስተማማኝና ትክክለኛ መረጃ በሚያስገኝለት መንገድ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነው።

እንደ (Lewy, 1979:163) ገለጻ ምልከታ ለተለያዩ ተግባራት ማለትም ለቡድን ስራ ፣ ለግል ስራ፣ ለሚና ጨዋታ፣ ለውይይት ወዘተ. መከፋፈሉን ለማየት ይረዳል። (Hancock, 1998: 89) ጨምረው እንደገለጹት አጥኚው በምልከታ የፈለገውንና ትክክለኛውን መረጃ የሚያገኝበት በመሆኑ ተፈላጊ የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያ ነው። በመሆኑም የተሻለ መረጃ ለማግኘት ነባራዊ የመማሪያ ክፍሉን፣ የመማር ማስተማር ሁኔታውን መመልከት ተገቢ ነው። በዚህም መሠረት አጥኚው የምልከታ ቅጽ /Observation checklist/ በማዘጋጀት ከትምህርት ቤቶቹ በተመረጡት ሴክሽኖች ላይ ምልከታ አካሂዷል። የምልከታ ቅጹ ከቀደምት ምሁራን ስራ ተነስቶ የተዘጋጀ ሲሆን በባለሞያ ተገምግሞ ስራ ላይ ውሏል፡፡ በዚህም መሠረት አጥኚው ተተኳሪ ምድቦችን ሁለት ሁለት ጊዜ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም በአጠቃላይ በአስራ ሁለቱ ምድቦች ላይ ሃያ አራት ምልከታዎችን አካሂዷል፡፡

### 3.2.2. የፅሁፍ መጠይቅ

የፅሁፍ መጠይቅ ለዚህ ጥናት ከተመረጡት የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች አንዱ ነው። የፅሁፍ መጠይቅ በአንድ ጊዜ ከብዙ ሰዎች ወይም ተጠኚዎች መረጃ ለማግኘት ከማስቻሉም በላይ ተጠኚዎች ያለምንም ስጋት የሚሰማቸውን ሀሳብ የሚገልጹበት እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን ገልጸዋል።

ለዚህ ጥናት የተዘጋጀው የጽሑፍ መጠይቅ ሁለት ክፍሎች ያሉት ነው። የመጀመሪያው ክፍል ዝግ ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን ለጥያቄዎቹ አምስት አምስት አማራጭ መልሶች ቀርበዋል። ለሁሉም ጥያቄዎች ወይም ሀሳቦች የቀረቡት አማራጮች ተመሳሳይ ናቸው።

እነሱም፡- 1 = በጣም አልስማማም
2 = አልስማማም
3 = መወሰን ያስቸግረኛል
4 = እስማማለሁ
5 = በጣም እስማማለሁ ናቸው።

ከእነዚህ አማራጮች አንጻር መላሾች ከጥያቄዎቹ ወይም ከሀሳቦቹ ትይዩ በሰንጠረዥ ካሉት አምስት ክፍት ቦታዎች በመረጡት አማራጭ ቁጥር ስር ይህንን (✓) ምልክት እንዲያስቀምጡ ተደርጓል። ነገር ግን በመረጃ ትንተና ሂደት አጥኚው ወደ ሶስት አጠጋግቷቸዋል። ይህም የሆነው የመረጃው ትንተና ሂደት ቀላልና ግልፅ እንዲሆን ስለተፈለገ ነው። በዚህም መሠረት ቁጥር 4 እና 5 እንደ አዎንታዊ ምላሽ ፣ ቁጥር 1 እና 2 እንደአሉታዊ መላሽ እንዲሁም ቁጥር 3 ለመወሰን የተቸገሩ በሚል ተወስደዋል። ሁለተኛው ክፍል ክፍት ጥያቄ ሆኖ መላሾች በነፃነት ከቀረበው ጥያቄ አንጻር የሚታያቸውን ሀሳብ እንዲሰነዝሩ የሚጋብዝ ነው። በዚህም መሠረት ገላጭ መልሶችን ለማገኘት ተችሏል። በዚህም መሠረት ገላጭ መልሶችን ለማገኘት ተችሏል።

በሰንጠረዥ አራት ላይ እንደተመለከተው አጠቃላይ ከሶስቱም ትምህርት ቤቶች ሶስት መቶ ስድስት ተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ሰላሳ ስምንቱ ወይም 12.4 በመቶ የወሰዱትን ወረቀት ሞልተው ያልመለሱ ሲሆኑ ሃያ ስድስቱ ወይም ከአጠቃላይ 8.5 በመቶ በግድየለሽነት ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ መልስ በመመለሳቸው ያልተወሰደላቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም አጠቃላይ የፅሁፍ መጠይቅ ከሞሉት ሶስት መቶ ስድሰት ተማሪዎች የሁለት መቶ ስልሳ ሁለት ተማሪዎች ብቻ ተቆጥሮ ተወስዷል።

### 3.2.3. ቃለመጠይቅ

ቃለ መጠይቅ ግልጽና ጥልቀት ያለው መረጃ ለማግኘት የሚያገለግል የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው። ይህንን አስመልክተው ያለው 1998 ፣ 2001 እንደገለጹት በቃለ መጠይቅ ወቅት የመላሹን አካላዊ እንቅስቃሴ፣ የፊትና የስሜት መለዋወጥ እንዲሁም ሌሎች ሁኔታዎችን ለመመልከትና ለማንበብ ስለሚያስችለው ተመራማሪው ከመላሹ የቃል መለሶች በተጨማሪ ቃል አልባ ምላሾችን ስለሚያገኝ ለምረምሩ ጥሩና አጋዥ የሆነ መረጃ ለመሰብሰብ ያሰችለዋል። በመሆኑም አጥኚው በምልከታና በፅሁፍ

መጠይቅ የተገኘውን መረጃ ለማጠናከር በተጨማሪነት ለተተኳሪ መምህራን ቃለ-መጠይቅ አካሂዷል። ለዚህም አጥኚው በመጀመሪያ ስምንት የቃል ጥያቄዎችን አዘጋጅቶ ነበረ ቢሆንም በባለሙያ የተስተካከሉ አራት ጥያቅዎችን ብቻ ለተተኳሪ መምህራን አቅረቧል፡፡

## 3.3. የመረጃ አተናተን ስልት

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በዚህ ጥናት አይነታዊና አሀዛዊ የአጠናን ዘዴዎች አገልግሎት ላይ ውሏል። በዚህም መሠረት በምልከታና በጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በአብዛኛው በአሀዝ የተተነተኑ ሲሆን በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በገለጻ ተተንተነዋል። በተጠቀሱት የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች በተገቢው ቦታ በማካተት በትንተናው ሂደት የተነሱትን ሀሳቦች ግልጽና ተጨባጭ ለማድረግ ተሞክሯል።

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተና

ይህ ምዕራፍ ለጥናቱ የተሰበሰቡ መረጃዎች ተተንትነው የሚቀርቡበት ነው፡፡ በዚህ መሠረት ከክፍል ውስጥ ምልከታ ቅጽ እና ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች ሰንጠረዦችን በመጠቀም ቀርበዋል፡፡ እነዚህ በሰንጠረዥ የቀረቡት አሃዛዊ መረጃዎች በገለፃ ተተርጉመዋል፡፡ በአንጻሩ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች በገለጻ ተተንትነዋል።

### 4.1. የተማሪ-ተኮር የማስተማር ዘዴዎች አተገባበር

በተተኳሪ ትምህርት ቤቶቹ ያለውን ተማሪ-ተኮር የማስተማሪያ ዘዴዎች ትግበራ በተመለከተ ከክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ታይቷል፡፡

ሰንጠረዥ አራት፡- ከምልከታ የተገኘ መረጃ

| ተ. ቁ. | ጥያቄ | ምላሾች | | | | አጠቃላይ የምልከታ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይደለም | | |
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | |
| 2.6. | መምህሩ የተለያዩ ተማሪዎችን የሚያሳትፉ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተጠቅሟል? | 5 | 20.8 | 19 | 79.2 | 24 |

ሰንጠረዥ አራት ላይ እንደተመለከተው የተማሪ-ተኮር የማስተማር ዘዴዎች አተገባበርን በሚመለከት ከምልከታ ቅጽ የተገኘ መረጃ ነው። አጥኚው በሶስቱ ትምህርት ቤቶች ሃያ አራት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለጊዜዎችን ተመልክቷል። በአጠቃላይ አጥኚው ምልከታ ካደረገባቸው ሃያ አራት ክፍለጊዜዎች በአምስቱ ብቻ መምህራን ተማሪዎችን የሚያሰትፉ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተጠቅመዋል። ይህም አጠቃላይ ምልከታ ከተደረገባቸው 20.8 በመቶ ክፍለጊዜዎች ናቸው። በአንጻሩ በተቀሩት አስራ ዘጠኝ ወይም ከአጠቃላይ 79.2 በመቶ ክፍለጊዜዎች መምህራን

በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አልተመቀሙም። ቀጣዩ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃም ይህንን ሃሳብ ያጠናክራል፡፡ በሰንጠረዥ ውስጥ የቀረቡት ተራ ቁጥሮች ሲሆኑ መጠይቅ ጥያቄዎቹ "አባሪ ሀ" ላይ ተካትተዋል፡፡

ሰንጠረዥ አምስት፡- የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ ሁኔታ /ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ/

| መጠይቆች ተ.ቁ. | ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የተገኙ ምላሾች | | | | | | | | | ከሶስቱ ትምህርት ቤቶች የተገኙ ምላሾች | | | | | | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከጊምቦ ት/ቤት | | | ከአውራዳ ት/ቤት | | | ከቢሻው ወ/ዮ ት/ቤት | | | አዎንታዊ ምላሽ | | ያልወሰኑ | | አሉታዊ ምላሽ | | |
| | አዎንታዊ | ያልወሰኑ | አሉታዊ | አዎንታዊ | ያልወሰኑ | አሉታዊ | አዎንታዊ | ያልወሰኑ | አሉታዊ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | |
| 1. | 29 | 4 | 57 | 33 | 5 | 42 | 27 | 8 | 57 | 89 | 33.9 | 17 | 6.5 | 156 | 59.6 | 262 |
| 6. | 36 | 7 | 47 | 38 | 6 | 36 | 39 | 7 | 53 | 113 | 43.1 | 20 | 7.6 | 137 | 49.3 | 262 |
| 10. | 28 | 10 | 52 | 31 | 9 | 40 | 38 | 9 | 55 | 97 | 37 | 27 | 10.3 | 138 | 52.7 | 262 |
| 11. | 25 | 2 | 63 | 30 | 8 | 52 | 41 | 4 | 47 | 96 | 36.6 | 14 | 5.3 | 152 | 58.1 | 262 |
| 12. | 29 | 8 | 63 | 33 | 4 | 43 | 25 | 4 | 63 | 87 | 33.2 | 16 | 6.1 | 159 | 60.7 | 262 |
| 14. | 36 | 6 | 48 | 26 | 4 | 50 | 37 | 9 | 46 | 99 | 37.7 | 19 | 7.2 | 153 | 55.1 | 262 |
| 15. | 32 | 2 | 56 | 19 | 10 | 51 | 22 | 3 | 65 | 93 | 35.5 | 15 | 5.7 | 154 | 58.8 | 262 |

ከፍ ሲል በሰንጠረዥ አምስት የተመለከቱት ጥያቄዎች በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ አተገባበርን ለመፈተሽ የቀረቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም ከጥያቄዎቹ ወይም ከሀሳቦቹ አንጻር ከየትምህርት ቤቶቹ የተገኙት መረጃዎች በተናጠል የቀረቡ ሲሆን ለእያንዳንዱ ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡትን የመልስ አሀዝ የያዘ ነው። በተጨማሪም በሰንጠረዡ ለአማራጮቹ /አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ፣ መወሰን የተቸገሩ፣ አሉታዊ ምላሽ ምን ያህል ምላሾች እንደተሰጡ የሚያሳይ አሀዝ እና መቶኛ ተገልጿል።

በሰንጠረዥ አምስት ላይ እንደተመለከተው በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ያለውን የአሳታፊ ትምህርት አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር ለሚጠይቁ ለእነዚህ ሰባት ጥያቄዎች ተማሪዎች በአብዛኛው አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በመጠይቅ ተራ ቁጥር 1 ላይ የቀረበው ጥያቄ ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተጠቅመው እየተማሩ እንደሆነ የሚጠይቅ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ከሶስቱ ትምህርት ቤቶች አንድ መቶ ሀምሳ ስድስት ተማሪዎች ወይም ከአጠቃላይ 59.6 በመቶ አሉታዊ ምላሽ የሰጡ ናቸው፡፡ በአንጻሩ ሰማንያ ዘጠኝ ተማሪዎች ወይም 33.9 በመቶ አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆኑ አስራ ሰባት ወይም 6.5 በመቶ ተማሪዎች ለመወሰን የተቸገሩ ናቸው። ከየትምህርት ቤቶቹ በተናጠል ያለውንም አሀዝ ስንመለከት መላሾች በአብዛኛው ለጥያቄው አሉታዊ መልስ እንደሰጡ የሚያሳይ ነው። በዚህ መሠረት በትምህርት ቤቶቹ ተማሪዎች የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ተጠቅመው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በአብዛኛው እየተማሩ እንዳልሆነ ገልጸዋል።

በተመሳሳይ መልኩ በተራ ቁጥር 6 ላይ የቀረበላቸው ጥያቄ ትምህርታቸውን በተግባር አስደግፈው ይማሩ እንደሆን የሚጠይቅ ነበር፡፡ ለዚህ ጥያቄ አንድ መቶ ሰላሳ ሰባት ወይም ከአጠቃላይ 49.3 በመቶ ተማሪዎች አሉታዊ ምላሽ ሲሰጡ አንድ መቶ አስራ ሶስቱ ወይም 43.1 በመቶ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። የተቀሩት ሃያ ወይም 7.6 በመቶ መላሾች ለመወሰን የተቸገሩ ናቸው። ከየትምህርት ቤቶቹም የተገኘው መረጃ ተናጠላዊ አሀዝ ሲታይ ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የአሉታዊ ምላሽ አሀዝ በልጦ ተገኝቷል። በዚህ መረጃ መሠረት በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በአብዛኛው የአማርኛ ቋንቋን በተግባር አስደግፈው እንደማይማሩ መግለጽ ችለዋል።

በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎችን በቡድን አደራጅቶ ማስተማር ተማሪዎችን ከሚሳትፉ የማስተማር ዘዴዎች አንዱ ነው። ይህ በቡድን ስራ የመማር ሂደት ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ሁሉም የቡድኑ አባላት በእኩል ደረጃ እንዲሳፉ ሲደረግ ነው። ይህንን ለማድረግ በቡድን ውስጥ ለተማሪዎች የተለያዩ ሚናዎችን መስጠት ወይም ማመቻቸት ያስፈልጋል። እያንዳንዱ የቡድኑ አባል የራሱ የሆነ ሚና ካለው ሚናውን በሚወጣበት ጊዜ በትምህርቱ ሂደት በንቃት ይሳተፋል ማለት ነው። ይህንን ለማረጋገጥ ለተማሪዎቹ በጽሁፍ መጠይቅ ተራ ቁጥር 10 ላይ ጥያቄ ቀርቦላቸዋል። ጥያቄውም “በቡድን ውስጥ ሁላችሁም የቡድኑ አባላት የየራሳችሁ ሚና/የአስተባባሪነት፣ የፀሀፊነት ፣ የጊዜ ተቆጣጣሪነነት ፣ የአቅራቢነት ወዘተ/ ተሰጥቷችኋል?” የሚል ነበር። ለዚህ ጥያቄ ከአጠቃላዩ ዘጠና ሰባት ወይም 37 በመቶ መላሾች አዎንታዊ ምላሽ የሰጡት ሲሆኑ አንድ መቶ ሰላሳ ስምንት ወይም 52.7 በመቶ ተማሪዎች አሉታዊ ምላሽ የሰጡ ናቸው። የተቀሩት ሃያ ሰባት ወይም ከአጠቃላዩ 10.3 በመቶ ተማሪዎች ለመወሰን የተቸገሩ ናቸው። በመሆኑም በቀረበው የአጠቃላይ አህዝ አሉታዊ መላሾች በልጠዋል። ከየትምህርት ቤቶቹ የተገኙትም ምላሾች በተናጠል ሲታዩ በሶስቱም ትምህርት ቤቶች ላይ አሉታዊ ምላሽ በአህዝ በልጦ ተገኝቷል። በዚህ መሠረት በትምህርት ቤቶቹ በቡድን ስራ ወቅት በአብዛኛው ለተማሪዎች ሚና ተለይቶ እንደማይሰጣቸው ማየት ይቻላል።

በተጨማሪም በመጠይቅ ተራ ቁጥር 12 ላይ የቀረበው ጥያቄ በቡድን ስራ ሂደት የተማሪዎችን ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው። ለዚህም ከአጠቃላዩ ሰማንያ ሰባት ወይም 33.2 በመቶ ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን አንድ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ወይም ከአጠቃላይ 60.7 በመቶ ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። በመሆኑም በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች በአብዛኛው ሁሉን አሳታፊ የሆነ የቡድን ስራ እንደማይከናወን ከተማሪዎቹ የተገኘው መረጃ ያሳያል።

የተማሪ-ተኮር የትምህርት ሂደት የተማሪዎች ትኩረትና ተሳትፎ የበዛበት ነው። በመሆኑም ትምህርቱ የተማሪዎችን ትኩረትና ንቁ ተሳትፎ ከሚያገኝባቸው ነገሮች አንዱ በቅድሚያ ተማሪዎች ለትምህርቱ እንዲነሳሱ/እንደነቃቁ ማድረግ ነው። ይንን ለማደረግ መምህራን ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት መቀስቀሻ /icebreaker/ መጠቀም ይጠበቅባቸዋል። በቅድሚያ ተማሪዎች እንዲነቃቁ ማድረግ የአሳታፊ

ትምህርት አንዱ ገጽታ ነው። ይህንን ሁኔታ ለመፈተሽ ለተማሪዎቹ በመጠይቅ ተራ ቁጥር 11 ላይ "ትምህርታችሁን ከመጀመራችሁ በፊት መቀስቀሻ ወይም ማነሳሻ ታገኛላችሁ?" የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸዋል። ለዚህ ጥያቄ ከአጠቃላዩ ዘጠና ስድስት ወይም 36.6 በመቶ ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን አንድ መቶ ሃምሳ ሁለት ወይም 58.1 በመቶ ተማሪዎች አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። የተቀሩት አስራ አራት ወይም 5.3 በመቶ ተማሪዎች ለመወሰን የተቸገሩ ናቸው። በመሆኑም በሶስቱም ትምህርት ቤቶች መምህራን በትምህርቱ መጀመሪያ በተማሪዎች ላይ ተነሳሶትን በመፍጠር ረገድ ያለው ሁኔታ አሉታዊ መሆኑን መየት ይቻላል።

ተማሪዎች በትምህርታቸው ሂደት የተለያዩ ችግሮችን እንዲፈቱ ማደረግ በትምህርታቸው ንቁ ተሳታፊ ለማድረግ ከሚጠቅሙ ዘዴዎች አንዱ ነው። በመሆኑም በሰንጠረዥ አራት ከተመለከቱት መረጃዎች ሌላው ተማሪዎች በትምህርታቸው ተጠቅመው የአካባቢያቸውን ችግር እንደፈቱ የሚጠይቅ ነው። ይህ ጥያቄ የቀረበው በሰንጠረዡ ውስጥ ተራ ቁጥር 14 ላይ ነው። ለዚህ ጥያቄ ዘጠና ዘጠኝ ወይም 37.7 በመቶ ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን አንድ መቶ ሃምሳ ሶስት ወይም 55.1 በመቶ ተማሪዎች አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። የተቀሩት አስራ ዘጠኝ ወይም ከአጠቃላዩ 7.2 መላሾች ለመወሰን የተቸገሩ ናቸው። በመሆኑም በጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች በአብዛኛው ተማሪዎች በትምህርታቸው የአካባቢያቸውን ችግር ለመፍታት እንዲጥሩ እንደማይደረግ ከመረጃው መረዳት ይቻላል።

የብጤ ትምህርት /peer teaching/ አንዱ የተማሪ-ተኮር የማስተማር ዘዴ ነው። ተማሪዎች በተለያዩ ይዘቶች ላይ ዝግጅት አድርገው አቻዎቻቸውን የሚያስተምሩበት ነው። በዚህ ዘዴ ተማሪዎች በተሰጣቸው ይዘት ላይ በቂ ዝግጅት አድርገው ስለሚቀርቡ በይዘቶች ላይ ጥልቅ ግንዛቤና በራስ መተማመንን እንዲያሳድት ይረዳቸዋል። በመሆኑም በትምህርት ቤቶቹ የዚህን አሳታፊ ዘዴ አተገባበር ለመለየት በመጠይቁ ውስጥ በተራ ቁጥር 15 ላይ ለተማሪዎች ጥያቄ ቀርቦላቸዋል። በመሆኑም ለጥያቄው ዘጠና ሶስት ወይም 35.5 በመቶ ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን አንድ መቶ ሃምሳ አራት ወይም ከአጠቃላይ 58.8 በመቶ ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። አስራ አምስቱ ደግሞ ለመወሰን የተቸገሩ ናቸው። ስለዚህ በትምህርት ቤቶቹ የአቻ ትምህርት በአብዛኛው እየተከናወነ እንዳልሆነ ከመረጃው

ማየት ይቻላል። በአጠቃላይ በሰንጠረዥ 4 ከተመለከተው መረጃ መገንዘብ የሚቻለው በተተኳሪ ትምህርት ቤቶቹ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለጊዜ አሳታፊ ዘዴን ከመጠቀም ፣ ተማሪዎችን በትምህርት ወቅት በቡድን ከማዋቀርና ለቡድን አባላት ሚና ከመስጠት፣ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ከመጀመራቸው በፊት ማነቃቂያ ከማግኘት ፣ ተማሪዎችን በትምህርታቸው ችግራቸውን እንዲፈቱ ከማድረግ ፣ እንዲሁም የአቻ ትምህርት ከማድረግ አንጻር ያለው ሁኔታ በአብዛኛው አሉታዊ ነው። በመሆኑም ከተተኳሪ ተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ በመነሳት በትምህርት ቤቶቹ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ አሳታፊ የማስተማር ዘዴ በአብዛኛው ተግባራዊ እየተደረገ እንዳልሆነ የሚያሳይ ነው፡፡

በተጨማሪም ከተተኳሪ መምህራን በቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ ከፍ ሲል የቀረበውን ሃሳብ ያጠነክራል፡፡

አጥኚው፡- አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ በተለያየ መልኩ ተጠቅመዋል?

መምህር ሀ፡- ቀደም ሲል እንዳልኩህ ለአቀራረቡ ጥሩ ግንዛቤ አለኝ፡፡ ነገር ግን ይህንን ያለው ሁኔታ ለመተግበር አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ በሀሳብ /theory/ ደረጃ ብቻ ነው፡፡ በክፍል ውስጥ አንተም እንደተመለከትከው ተማሪዎች ፍላጎት የላቸውም፡፡ ተማሪዎቹ በአብዛኛው ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል አማርኛ የሁለተኛ ቋንቋቸው ስለሆነ አድርጉ የሚባሉትን ነገር ለማከናወን ይቸገራሉ፡፡

መምህርት ለ ፡- አዎ…… ብቻ …. በተወሰነ መልኩም ቢሆን እየተጠቀምኩ ነኝ ማለት እችላለሁ፡፡ ምክንያቱም አሳታፊ አቀራረብ የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂል ለማዳበር እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡

መምህር ሐ ፡- በአብዛኛው ባይሆንም ተጠቅሜያለሁ፡፡

መምህር መ፡- አዎ በተቻለኝ መጠን አልፎ አልፎ እንጠቀማለን።

መምህር ሠ፦ በተገቢው ሁኔታ ተጠቅሚያለሁ ማለት ያስቸግረኛል። ነገር ግን የተለያዩ እንቅፋቶች ቢኖሩትም መጠቀም ግድ ስለሆነ አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ።

መምህር ረ፦ ተጠቅሜያለሁ።

ቀደም ሲል የቀረበው የቃለ መጠይቅ መረጃ ተተኳሪ መምህራን በክፍላቸው ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን እየተጠቀሙ እንደሆነ ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ ነው፡፡ እነዚህ መምህራን ከሶስቱም የጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የተወሰዱ ናቸው፡፡ በምላሻቸውም አሳታፊ ዘዴን በትምህርት ክፍላቸው ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ እንደማይጠቀሙ ገልፀዋል፡፡ በተለያዩ ችግሮች ምክንያት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ መጠቀም እንዳልቻሉ ተናግረዋል። በመሆኑም ይህ መረጃ ቀደም ሲል በፅሁፍ መጠይቅ የተገኘውን ሀሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡ ስለዚህ በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሳታፊ የማስተማር ዘዴ በአገልግሎት ላይ እየዋለ እንዳልሆነ የሚያመላክት ነው፡፡ በመሆኑም ቀደም ሲል በተከታታይ ምልከታ ፣ በጽሁፍ መጠይቅና በቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በትምህርት ቤቶቹ አሳታፊ የትምህርት አቀራረብ በተገቢው ሁኔታ እየተተገበረ እንዳልሆነ ማረጋገጥ ይቻላል።

## 4.2. በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የመምህራንና የተማሪው ሚና

በተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ሂደት መምህሩና ተማሪው የራሳቸው የሆነ ሚና አላቸው፡፡ በዚህ አቀራረብ ተማሪው የትምህርቱ ማዕከል ቢሆንም መምህሩ የራሱ የሆነ ሚና አለው፡፡ በክፍል ተማሪዎች ለትምህርቱ እንዲነሳሱ ትኩረት ሰጥተው እንዲከታተሉት እንዲሁም የተሰጣቸውን ተግባር በአግባቡ እንዲያከናውኑ ማድረግ ይጠበቅበታል። ይህንን አስመልክቶ በካፋ ዞን በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ያለውን የመምህሩንና የተማሪውን ሚና በተመለከተ በተለያዩ መንገዶች የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

### 4.2.1 የመምህራን ሚና በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች

በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ በማደረግ በክፍል ውስጥ ያለውን የመምህሩን ሚና የሚመለከት መረጃ ማግኘት ተችሏል። ይህም የተከናወነው በምልከታ ቅጽ አማካይነት ተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ በማድረግ ነው።

ሰንጠረዥ ስድስት፡- በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የመምህሩ ሚና /የምልከታ መረጃ/

| ተ.ቁ | ክንውን | ምላሾች | | | | አጠቃላይ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይደለም | | |
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | |
| 2.1 | የትምህርቱን ርዕስ አስተዋውቋል | 20 | 83.3 | 4 | 16.7 | 24 |
| 2..2 | የትምህርቱን አላማ ገልጿል | 1 | 4.1 | 23 | 95.9 | 24 |
| 2.3 | ተማሪዎችን ለተግባራት አደራጅቷል | 0 | 0 | 24 | 100 | 24 |
| 2.4 | የተማሪዎቹን ሚና አሳውቋል | 0 | 0 | 24 | 100 | 24 |
| 2.5 | ተማሪዎችን አነሳስቷል | 1 | 4.1 | 23 | 95.9 | 24 |
| 2.6 | የተለያዩ አሳታፊ ዘዴዎችን ተጠቅሟል | 5 | 20.8 | 19 | 79.2 | 24 |
| 2.7 | የቡድን ስራ ሰጥቷል | 3 | 12.5 | 21 | 77.5 | 24 |
| 2.8 | በቡድን ውስጥ ተማሪዎች አሳትፏል | 1 | 4.1 | 23 | 95.9 | 24 |
| 2.9 | የተማሪዎቹን ግንዛቤና እውቀት ገምግሟል | 16 | 66.6 | 8 | 33.4 | 24 |
| 2.10 | ለተማሪዎች መልመጃ ሰጥቷል | 11 | 45.8 | 13 | 54.2 | 24 |
| 2.11 | ተማሪዎች ጥያቄውን እንዲመልሱ በቂ ዕድል ሰጥቷል፡፡ | 2 | 8.3 | 22 | 9.7 | 24 |

በሰንጠረዥ ስድስት ላይ እንደተመለከተው በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያለውን የመምህራን የክፍል ውስጥ ሚና አጥኚው በምልከታ ቅፅ አማካይነት ተመልክቷል፡፡

በዚህም መሠረት ምልከታ ከተካሄደባቸው ሃያ አራት ክፍል ጊዜዎች በሃያዎቹ መምህራን የዕለቱን ትምህርት ርዕስ ለተማሪዎቻቸው ገልፀዋል፡፡ በአንፃሩ በአራቱ ክፍል ጊዜዎች መምህራን የዕለቱን ትምህርት ርዕስ ለተማሪዎቻቸው አልገለፁም፡፡ በመሆኑም በመረጃው መሠረት ምልከታ ከተካሄደባቸው ክፍለጊዜዎች በአብዛኛው ወይም 83.3 በመቶ ክፍለጊዜዎች መምህራን የትምህርት ርዕሳቸውን ለተማሪዎቻቸው አሳውቀዋል፡፡ ነገር ግን መምህራን የዕለቱን ትምህርት አላማ ለተማሪዎቻቸው በመግለፅ ረገድ ምልከታ ከተደረገባቸው ሃያ አራት ክፍለጊዜዎች በአብዛኛዎቹ አላከናወኑም፡፡ በዚህም መሠረት አጥኚው ምልከታ ካደረገባቸው ሃያ አራት ክፍል ጊዜዎች በአንዱ ብቻ የትምህርቱ ዓላማ ለተማሪዎች ሲገለፅ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም በሃያ ሶስቱ ክፍል ጊዜዎች ማለትም ከአጠቃላዩ 95.9 በመቶ ክፍል ጊዜዎች መምህራን የትምህርት አላማቸውን ለተማሪዎቻቸው አልገለፁም፡፡ ስለዚህ ከተገኘው መረጃ በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች መምህራን በአብዛኛው የዕለቱን ትምህርት አላማ ለተማሪዎቻቸው አይገልፁም ወደሚል መደምደሚያ መድረስ ይቻላል፡፡

ሌላው መምህሩ በክፍል ጊዜው ተማሪዎች የሚያከናውኗቸውን ተግባራት መግለጽ ይጠበቅበታል። ይህ ተማሪዎች የሚያደርጉትን አውቀው ቀድመው እንዲዘጋጁ ይረዳቸዋል። በመሆኑም በሰንጠረዥ ሰባት ጥያቄ ቁጥር 2.4. ላይ የቀረበው ጥያቄ ይህንን ለማረጋገጥ የቀረበ ነው። ሆኖም ምልከታ በተካሄደባቸው ሁሉም ክፍል ጊዜዎች መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው በክፍል ጊዜው የሚያከናውኗቸውን ተግበራት አልገለፁላቸውም/አላሳወቋቸውም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ መምህራን ተማሪዎችን ለተለያዩ ተግበራት አላደራጇቸውም፡፡ አጥኚው በተመለከታቸው ሁሉም ክፍል ጊዜዎች መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለተለያዩ ተግባራት ወይም ሚናዎች አላደራጁም፡፡ በተጨማሪም በሰንጠረዥ ሶስት በጥያቄ ቁጥር 2.5 ከቀረበው “ተማሪዎች ትምህርቱን በፍላጐትና በትኩረት እንዲከታተሉ አነሳስቷቸዋል?” ጥያቄ አንፃር አጥኚው ከሁሉም ተተኳሪ ክፍለጊዜዎች በሁሉም አሉታዊ ምላሽ አግኝቷል፡፡ በመሆኑም ከዚህ መረጃ የተተኳሪ ትምህርት ቤቶች መምህራን የተማሪዎችን ፍላጐትና ትኩረት ለማግኘት መቀስቀሻ ወይም ማነሳሻ ዘዴዎችን አይጠቀምም የሚል መደምደሚያ መስጠት ይቻላል፡፡

በሰንጠረዥ ስድስት ከተመለከቱት መረጃዎች አንዱ መምህራን ተማሪዎችን የሚያሳትፉ የተለያዩ አሳታፊ ዘዴዎችን እንደተጠቀሙ የሚጠይቅ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በሶስቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች አጥኚው ምልከታ ካደረገባቸው ክፍለ ጊዜዎች መምህራን በአምስቱ ወይም ከአጠቃላዩ 20.8 በመቶ የተለያዩ አሳታፊ ዘዴዎችን ተጠቅመዋል፡፡ በአንፃሩ በአስራ ዘጠኝ ክፍለ ጊዜዎች ወይም ከአጠቃላዩ 79.2 በመቶ ክፍለጊዜዎች መምህራን የተለያዩ አሳታፊ ዘዴዎችን አዋህደው አልተጠቀሙም፡፡ ከዚህ አንፃር የትምህርት ቤቶቹ መምህራን በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን ንቁ ተሳታፊ የሚያደርጉ አሳታፊ ዘዴዎች እንደማይጠቀሙ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን በቡድን ማሰራት እንዲሁም በቡድኑ ውስጥ ተማሪዎች የሚኖራቸውን ተሳትፎ መከታተል የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በዚህም አጥኚው ከተመለከታቸው ሃያ አራት ክፍለ ጊዜዎች መምህራን ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ የቡድን ስራ ያሰሩት በሶስቱ ክፍለጊዜዎች ብቻ ነው፡፡ በተቀሩት ሃያ አንድ ወይም ከአጠቃላይ 87.5 በመቶ ክፍለ ጊዜዎች መምህራን ተማሪዎችን በቡድን ስራ አላሰሩም፡፡ የቡድን ስራ ከተሰጠባቸውም ሶስት ክፍለ ጊዜዎች የቡድኑ አባላት በትክክል መሳተፋቸው ክትትል የተደረገው በአንዱ ክፍለ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ይህም የአጠቃላይ ምልከታ ከተደረገባቸው 4.1 በመቶ ብቻ መሆኑ ነው፡፡ በአንፃሩ በቀሩት በሃያ ሶስቱ ወይም ከአጠቃላዩ 95.9 በመቶ ክፍለ ጊዜዎች መምህራን በቡድን ስራ ወቅት ተማሪዎቻቸውን አልተከታተሉም፡፡ በመሆኑም ከዚህ መረጃ መሠረት በትምህርት ቤቶቹ መምህራን በአብዛኛው ተማሪዎቻቸውን የቡድን ስራ እንደማያሰሩና በቡድን ውስጥ ተማሪዎች ያላቸውን ተሳትፎ እንደማይቆጣጠሩ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ሌላው በሰንጠረዥ ስድስት ከቀረቡት ጥያቄዎች አንዱ በተራ ቁጥር 2.9. ላይ የቀረበው ነው፡፡ ይህ ጥያቄ መምህሩ የተማሪዎችን ግንዛቤና ክሂል ለመለየት ጥያቄ መጠየቁን የሚመለከት ነው፡፡ ከዚህ ጥያቄ አንፃር ምልከታው ከተካሄደባቸው ሃያ አራት ክፍለ ጊዜዎች በአስራ ስድስቱ ወይም ከአጠቃላዩ 66.6 በመቶ ክፍለጊዜዎች መምህራን በትምህርቱ ማጠቃለያ ላይ ጥያቄ የጠየቁ ሲሆን በስምንቱ ወይም 33.4 በመቶው ጥያቄ ያልተጠየቀባቸው ናቸው፡፡

ሌላው በሰንጠረዥ ስድስት በተራ ቁጥር በ2.10 ላይ የተቀረበው "መምህሩ ለተማሪዎች የቡድን ስራ፣ የቤት ስራ በአጠቃላይ ለመለማመጃ የሚሆኑ ጥያቄዎችን ሰጥቷል?"

የሚል ጥያቄ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ምልከታ ከተደረገባቸው ከሃያ አራት ክፍለ ጊዜዎች በአስራ አንዱ ክፍለ ጊዜዎች መምህራን ለተማሪዎቻቸው ልምምድ የሚሆኑ የቤት ስራዎችን ሰጥተዋል። ነገር ግን በአስራ ሶስቱ ወይም ከአጠቃላይ 54.2 ክፍለጊዜዎች መምህራን ለተማሪዎቻቸው መለማመጃ የሚሆኑ ሰራዎችን አልሰጡም። በሌላ በኩል ሰንጠረዡ ውስጥ 2.11. ላይ የቀረበው ጥያቄ "መምህሩ ያቀረባቸውን ጥያቄዎች ራሱ ከመመለስ ይልቅ ለተማሪማዎች በቂ ዕድል ሰጥቷቸዋል?" የሚል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አጥኚው ከተመለከታቸው ክፍለ ጊዜዎች በሁለቱ ብቻ መምህራን ለተማሪዎች መልሰ በቂ እድል ሰጥተዋተዋል፡፡ በተቀሩት በሃያ ሁለቱ ማለትም በ91.7 በመቶ ክፍለ ጊዜዎች መምህራን ተማሪዎች ጥያቄዎችን እንዲመልሱ በቂ ዕድል አልሰጧቸውም፡፡ በዚህ መሠረት በክፍለ ጊዜዎች አብዛኛዎቹ ተተኳሪ መምህራን ተማሪዎቻቸው የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ በቂ ዕድል አልሰጧቸውም ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ከመረጃው መምህራን በአብዛኛው ለተማሪዎች በቂ ጥያቄ የመመለስ እድል አይሰጡም ወደሚል መደምደሚያ መድረስ ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ሰንጠረዥ ስድስት ላይ የተመለከተው መረጃ በምልከታ ቅፅ የተገኘ ሲሆን በትምህርት ቤቶቹ በተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ሂደት መምህራን የሚኖራቸውን ሚና የሚመለከት ነው፡፡ መረጃው እንደሚያመለክተው የጥያቄዎቹ ምላሾች በአብዛኛው አሉታዊ ናቸው፡፡ ይህም መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ተገቢውን ሚናቸውን በአብዛኛው እየተወጡ እንዳልሆነ ያመለክታል፡፡

### 4.2.2. የተማሪው ሚና

በተማሪ ተኮር የትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች የራሳቸው የሆነ ሚና አላቸው፡፡ በዚህ ጥናት በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች በተማሪ ተኮር አቀራረብ ያለውን የተማሪዎች ሚና በተለያዩ መንገዶች ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በሰንጠረዥ አራት የቀረበው መረጃ ምልከታ ክፍል ውስጥ ምልከታ በማድረግ የተገኘ ነው፡፡ በሰንጠረዡ ላይ የተመለከተው ከተማሪዎች ሚና አንፃር የተደረገ የምልከታ ውጤት ነው፡፡

ሰንጠረዥ ሰባት፡- የተማሪዎች ሚና

| ተ.ቁ. | የተማሪዎች ሚና | ምላሽ | | | | አጠቃላይ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይደለም | | |
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | |
| 3.1. | ተማሪዎች በችግር ፈቺ ተግባራት ላይ ይሳተፋሉ? | 0 | 0 | 24 | 100 | 24 |
| 3.2. | ተማሪዎች ሚናዎችን ይጫወታሉ ወይም ይወጣሉ? | 0 | 0 | 24 | 100 | 24 |
| 3.3. | ተማሪዎች በቡድን ይወያያሉ? | 3 | 12.5 | 21 | 77.5 | 24 |
| 3.4. | ተነሳሶትን በመፍጠር ረገድ ተማሪዎች ድርሻ አላቸው? | 0 | 0 | 24 | 100 | 24 |
| 3.5. | ተማሪዎች በቡድን ውስጥ የስራ ድርሻ ተሰጥቷቸዋል? | 0 | 0 | 24 | 100 | 24 |
| 3.6. | የቡድን ውሰጥ የስራ ድርሻቸውን በአግባቡ ተወጥተዋል? | 1 | 4.1 | 23 | 95.9 | 24 |
| 3.7. | ጥያቄዎችን ጠይቀዋል? | 15 | | 9 | | 24 |
| 3.8. | የቃል ጥያቄ ለመመለስ ሁሉም ተማሪዎች ተሳትፎ ያደርጋሉ? | 0 | 0 | 24 | 100 | 24 |
| 3.9. | ተማሪዎች በንቃት ይሳተፋሉ? | 0 | 0 | 24 | 100 | 24 |

በተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች ማዕከላዊ ተሳታፊዎች ናቸው። በመሆኑም ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት የተለያዩ ሚናዎችን እንዲወጡ ይጠበቃል። በሰንጠረዥ ሰባት ውስጥ ከተራ ቁጥር 3.1 እስከ 3.9 የተጠቀሱት ሀሳቦች በተማሪ-ተኮር ወይም በአሳታፊ አቀራረብ የተማሪዎችን ሚና የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በመሆኑም በሰንጠረዡ ውስጥ በተራ ቁጥር 3.1 የቀረበው ጥያቄ ተማሪዎች በተለያዩ ችግር ፈቺ ተግባራት ላይ እንደተሳተፉ የሚጠይቅ ነው፡፡ ከዚህ ሃሳብ አንፃር ምልከታ በተደረገባቸው የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ምንም ዓይነት ችግር ፈቺ ተግባራት ተማሪዎች አልተሳፉም፡፡ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተለያዩ መልመጃዎች ተሰጥተዋቸው ለመፍታት እንዲጥሩ አልተደረጉም፡፡ ይህ የሚያመለክተው በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች በአብዛኛው የተለያዩ ችግር ፈቺ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ተማሪዎች እንዲማሩ የማድረግ ሂደት እንደሌለ ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች የተለያዩ

ሚናዎችን እንዲወጡ ወይም እንዲጫወቱ አልተደረገም፡፡ በመሆኑም አጥኚው ምልከታ ባደረገባቸው ክፍሎች ምንም ዓይነት የተማሪዎች የሚና ጨዋታ አልተከናወነም፡፡

በቡድን ስራ ወቅት ሁሉም የቡድኑ አባላት የየራሳቸው የሆነ የስራ ድርሻ ሊሰጣቸው ይገባል። የቡድን ስራ ውጤታማ የሚሆነው ሁሉም የቡድኑ አባላት በእኩል ደረጃ መሳተፍ ሲችሉ ነው።ይህ ካልሆነ የጥቂት ሰዎች ብቻ የበላይነት ያለበት ሊሆን ይችላል። በመሆኑም ሁሉም የቡድኑ አባላት ተመጣጣኝ የሆነ ግንዛቤ አያገኙበትም። ከዚህ አንጻር በሰንጠረዥ ስምንት በተራ ቁጥር 3.5. ላይ በቀረበው ጥያቄ መሠረት ምልከታ በተደረገባቸው ክፍለጊዜዎች መምህራን ለተማሪዎች በቡድን ስራ ወቅት ለእያንዳንዱ የቡድኑ አባላት የስራ ድርሻ አልተሰጣቸውም፡፡ በመሆኑም የተወሰኑ ሰዎች ብቻ አጠቃላይ የድድኑን ስራ እንዲያከናውኑ ሆኗል፡፡ የተቀሩት ሌሎች ደግሞ ለዘብተኛ ተመልካቾች ነበሩ፡፡ በመሆኑም በሰንጠረዥ 4 ጥያቄ ቁጥር 3.6 ላይ እንደተመለከተው አጥኚው ሃያ አራት ምልከታዎች ለአንዱ ብቻ ተማሪዎች በቡድን ውስጥ የስራ ድርሻቸውን እንዲወጡ ጥረት ተደርጓል፡፡ በአንፃሩ በተቀሩት በሃያ ሶስቱ ክፍል ጊዜዎች ላይ ይህ ሁኔታ አልተከናወነም፡፡

ሌላው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች ጥያቄ መጠየቅ አንዱ ሚናቸው ነው፡፡ በመሆኑም ምልከታ ከተካሄደባቸው ክፍለ ጊዜዎች በአስራ አምስቱ ተማሪዎች መምህራቸውን ጥያቄ ጠይቀዋል፡፡ በአንፃሩ በዘጠኙ ክፍለ ጊዜዎች ተማሪዎች ምንም ጥያቄ አልጠየቁም፡፡ በሌላ በኩል ምልከታ በተደረገባቸው በሁሉም ክፍለ ጊዜዎች የተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እጅ አውጥተው መልስ መልሰዋል፡፡ በአብዛኛው ግን አልተሳተፉም፡፡ በዚህም መሠረት አጥኚውም በተመለከታቸው ሃያ አራት ክፍል ጊዜዎች በሁሉም አብዛኛው የክፍሉ ተማሪዎች አልተሳተፉም፡፡ በዚህም መምህራን የሚያሳትፉት ተማሪዎች ፍላጎት ያላቸውን የተወሰኑት ተማሪዎች ብቻ ነው። በመሆኑም አብዛኞቹ ተማሪዎች ለዘብተኛ ተመልካቾች ሆነዋል። ከዚህ መረጃ በመነሳት በትምህርት ቤቶቹ በተማሪ-ተኮር የማስተማር ሂደት ተማሪዎች በአብዛኛው ሚናቸውን አልተወጡም ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

## 4.3. የመማሪያ ክፍሎች አደረጃጀት

በአሳታፊ ዘዴ የመማር ማስተማር ሂደት የመማሪያ ክፍሉ ያለው አደረጃጀት ወሳኝ ነው፡፡ ይህም በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎችን ንቁ ተሳታፊ ለማድረግ በወጉ የተደራጀ የመማሪያ ክፍል ሊኖር ይገባል፡፡ ይህም ማለት በክፍሉ ውስጥ ለተማሪዎች በቂ የሆኑ የመቀመጫ ወንበሮች ሊኖሩ ይገባል፡፡ ምክንያቱም በወንበር እጥረት ተጨናንቀው የተቀመጡ ተማሪዎች ለመሳተፍ ስለሚያስቸግራቸው ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተለያዩ ቡድኖችን አደራጅቶ ተማሪዎችን በቡድን ለማወያየት እንዲያመች ወንበሮቹ ተንቀሳቃሽ መሆን አለባቸው፡፡ በመሆኑም ከነዚህ ሁኔታዎች አንፃር አጥኚው ከተተኳሪ ትምህርት ቤቶች በምልከታ ያገኘው መረጃ ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

ሰንጠረዥ ስምንት፡- የክፍል አደረጃጀት

| ተ.ቁ | የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ | ምላሾች | | | | አጠቃላይ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይደለም | | |
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | |
| 1.1 | ለሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች በቂ የመቀመጫ ወንበሮች አሉ? | 4 | 33.3 | 8 | 66.7 | 12 |
| 1.2 | መቀመጫዎቹ ተንቀሳቃሽ ናቸው? | 1 | 8.3 | 11 | 91.7 | 12 |

በሰንጠረዥ ስምንት ላይ የተመለከተው በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች አጥኚው ምልከታ ባደረገባቸው አስራ ሁለት የመማሪያ ክፍሎች ያለውን የክፍል አደረጃጀት ሁኔታ ነው፡፡ ይህም የክፍሎቹ የመቀመጫ ወንበሮች አሳታፊ ወይም ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴዎችን ለመተግበር ምን ያህል ምቹ እንደሆኑ የሚያመለክት ነው፡፡ በተራ ቁጥር 1.1 የቀረበው ጥያቄ በክፍሉ ውስጥ ያሉ የመቀመጫ ወንበሮች ለተማሪዎች በቂ እንደሆኑ የሚጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም ምልከታ ከተደረገባቸው አስራ ሁለት ክፍሎች አራቱ ብቻ ለክፍሉ ተማሪዎች በቂ ወንበር ያላቸው ሲሆን የተቀሩት ስምንቱ በወንበር እጥረት ምክንያት ተማሪዎች ተጨናንቀው ተቀመጡባቸው ናቸው፡፡ በዚህ መሠረት ከአጠቃላይ ክፍሎቹ 33.3 በመቶ በቂ ወንበር ያላቸው ሲሆን 66.7 በመቶ ክፍሎች ደግሞ ለክፍሉ ተማሪዎች በቂ ወንበር የሌላቸው ናቸው፡፡ በዚህም በትምህርት ቤቶቹ የመማሪያ ክፍሎች በአብዛኛው የወንበር እጥረት እንዳለ ከተገኘው መረጃ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በመማሪያ ክፍል ውስጥ የመቀመጫ ወንበሮች ለተማሪዎች በቂ ከመሆን ባሻገር ተንቀሳቃሽ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ይህም መማሪያ ክፍሉን የተለያዩ የቡድን ስራዎችን ለማሰራት እንዲሁም በተለያዩ ጊዜ የተለያዩ ቡድኖችን አደራጅቶ ለማሰራት ምቹ ስለሚያደርገው ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ በሰንጠረዥ ዘጠኝ በተራ ቁጥር 1.2 የቀረበው ጥያቄ በመማሪያ ክፍሎቹ ውስጥ ያሉት ወንበሮች ተንቀሳቃሽ እንደሆኑ የሚጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚው ምልከታ ካደረገባቸው አስራ ሁለት የመማሪያ ክፍሎች አንዱ ከአጠቃላዩ 8.3 በመቶ ብቻ አዎንታዊ ምላሽ አግኝቷል፡፡ በአንፃሩ አጥኚው ከተመለከታቸው አስራ አንዱ ወይም 91.7 በመቶ የመማሪያ ክፍሎች አዎንታዊ ምላሽ የተገኘባቸው ናቸው፡፡ ይህ የሚያመለክተው ምልከታ ከተደረገባቸው ክፍሎች አብዛኞቹ ያላቸው የተማሪዎች መቀመጫ ወንበሮች የማይንቀሳቀሱ ወይም ለማንቀሳቀስ አስቸጋሪ መሆናቸውን ነው፡፡

የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ባሉት ወንበሮች መካከል በቂ የመተላለፊያ ቦታ መኖር የክፍል አደረጃጀት አንዱ ገፅታ ነው፡፡ ምክንያቱም በመቀመጫዎች ወንበሮች መካከል የሚኖረው ቦታ መምህራን በክፍል ውስጥ በነፃነት እየተዘዋወሩ የተማሪዎቻቸውን ስራና ተሳትፎ እንዲመለከቱና እንዲቆጣጠሩ ስለሚያስችል ነው፡፡ ይህንን አስመልክቶ ከአጥኚው የክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘ መረጃ በሰንጠረዥ ላይ ዘጠኝ ተመልክቷል፡፡

ሰንጠረዥ ዘጠኝ፡- ከምልከታ ቅፅ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ | ምላሾች | | | | አጠቃላይ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይደለም | | |
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | |
| 1.3 | በመቀመጫ ወንበሮች (Desk) መካከል በቂ የመተላለፊያ ቦታ አለ? | 5 | 41.6 | 7 | 58.4 | 12 |

በሰንጠረዥ ዘጠኝ ላይ የተመለከተው መረጃ ከክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘ ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚው ከተተኳሪ ትምህርት ቤቶች በአስራ ሁለት የመማሪያ ክፍሎች ምልከታ አድርጓል፡፡ በዚህም በሰንጠረዡ ላይ እንደተመለከተው በመማሪያ ክፍሎች የተማሪዎች የመቀመጫ ወንበሮች መካከል በቂ የመተላለፊያ ቦታ መኖሩን የሚጠይቅ

ጥያቄ ቀርቧል፡፡ ምልከታ ከተደረገባቸው አስራ ሁለት ክፍሎች አምስቱ ወይም ከአጠቃላይ 41.6 በመቶ ክፍሎች አዎንታዊ ምላሽ ያገኙ ሲሆን የተቀሩት ሰባቱ ወይም 58.4 በመቶ ክፍሎች አሉታዊ ምላሽ የተገኘባቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም በተገኘው መረጃ መሠረት በአብዛኞቹ የመማሪያ ክፍሎች በመቀመጫ ወንበሮች መካከል በቂ የመተላለፊያ ቦታ የሌላቸው መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡በዚህ መረጃ መሠረት በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ያለው የክፍል አደረጃጀት ተማሪ-ተኮር የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር አመቺ ያለመሆኑን ማየት ይቻላል። በሌላ በኩል ከተተኳሪ መምህራን የተገኘው የቃለመጠይቅ መረጃ ይህንን ሃሳብ የሚያጠናክርነው።

የመማሪያ ክፍሎች አደጃጀት የተማሪ-ተኮር የማስተማሪያ ዘጌዎችን ለመተግበር ያመቻል?

መምህር ሀ፦ የተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ ለማካወን በርካታ ቁሳቁሶችን ማሟላት ያስፈልጋል። የተለየዩ ቁሳቁሶች መሟላት አለባቸው፣ ቋንቋው ራሱን የቻለ ቤተ-ሙከራ ሊኖረው ይገባል። ይሁን እንጂ እንደተመለትከው በክፍል ውስጥ ተማሪዎች የሚቀመጡት ተጨናንቀው ነው።

መምህር ለ፦ በአብዛኛው አይመችም። ምክንያቱም በመማሪያ ክፍሉ ሁሉም ነገር የተመቻቸ አይደለም።

መምህር ሐ፦ አይመችም። የወንበር እጥረት አለ። ለሎችም ብዙ ችግሮች አሉ።

መምህር መ፦ አይመችም። ምክንያቱም የመማሪያ ክፍሉ አደረጃጀት አሳታፊ ዘዴዎችን ለመጠቀም አስቸጋሪ ነው።

መምህር ሠ፦ የክፍል ጥበት ፣ የመቀመጫ ወንበር እጥረት ስላለ አይችም።

መምህር ረ፦ በክፍል ውስጥ ያለው የወንበር አቀማመጥ ተማሪዎችን ለማሳተፍ አመቺ አይደለም።

ከፍ ሲል የቀረበው ከተተኳሪ መምህራን ቃለመጠይቅ የተገኘ ነው። በመሆኑም ሁሉም መምህራን መማሪያ ክፍሎች አደረጃጀት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመጠቀም

አመቺ ያለመሆኑን ገልፀዋል። ለዚህም የተለያዩ ችግሮችን ጠቅሰዋል። በዚህም መሰረት ቀደም ሲል የቀረበውን የክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃ የሚያጠናክር ነው። በአጠቃላይ ከምልከታውና ከቃለመጠይቅ መረጃዎች በመነሳት በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የመማሪያ ክፍሎች አደረጃጀት ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ በአብዛኛው አመቺ አይደለም ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

## 4.4. በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የተማሪ-ተኮር አቀራረብን በሚገባ ለመተግበር ብዙ ሁኔታዎች ሊመቻቹ ይገባል። ከዚህ አንጻር በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች አቀራረቡን በመተግበር ሂደት ችግሮች ይኖሩ እንደሆን ለመፈተሽ ተሞክሯል። በዚህም ለተተኳሪ ተማሪዎች በፅሁፍ መጠይቅ በቀረበ ክፍት ጥያቄ ፣ ለመምህራን በቀረበ ቃለ መጠይቅ እንዲሁም አጥኚው የክፍል ውስጥ ምልከታ በሚያደርግበት ወቅት አቀራረቡን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ሁኔታዎችን ተመልክቷል። ቀጥሎ እነዚህ መረጃዎች በቅደም ተከተል ይቀርባሉ።

ለተማሪዎች በቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ ክፍል ሁለት ላይ ክፍት ጥያቄዎች ተካተዋል። በመኑም ከጥያቄዎቹ በተራ ቁጥር 2 ላይ "በተማሪ ተኮር አቀራረብ የቋንቋ ትምህርቱን ስትማሩ ለምሳሌ በቡድን ወይይት፣ በጥንድ ስራ፣ በግል ስራ ጊዜ ያጋጠሟችሁ ችግሮች ዘርዝረው ይፃፉ።" የሚል ጥያቄ ቀርቧል። በዚህም መሠረት ከተማሪዎቹ የተገኙት ዝርዝር ምላሾች እንደሚያመለከቱት በክፍል ውስጥ የወንበር እጥረት ፣ የተማሪዎች ብዛት ፣ የመማሪያ መፃህፍት ያለመሟላት ፣ በቡድን ስራ ወቅት የጊዜ እጥረት ፣ የተማሪዎች በጋራ ተስማምቶ ያለመስራት ፣ የቡድን ስራ ሲሰጥ የሚሞክር ተማሪ ብቻ መስራትና በቡድን ስራ ወቅት ተማሪዎች ሀሳብ ያለመቀባበል የሚሉት በተማሪዎቹ የተጠቀሱ ችግሮች ናቸው።

በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች አሳታፊ የማስተማር ዘዴዎችን ለመተግበር የሚያደናቅፉ ችግሮችን በተመለከተ በክፍል ውስጥ መልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ አስራ አንድ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ አስር፦ አሳታፊ ዘዴዎችን ለመተግበር የሚገጥሙ ችግሮች

| ተ.ቁ. | የምልከታ ነጥቦች | ምላሽ | | | | አጠቃላይ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይደለም | | |
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | |
| 1.1. | ለሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች በቂ የመቀመጫ ወንበሮች አሉ? | 4 | 33.3 | 8 | 66.7 | 12 |
| 1.2. | መቀመጫዎቹ ተንቀሳቃሽ ናቸው? | 1 | 8.3 | 11 | 91.7 | 12 |
| 1.3. | የመማሪያ ክፍሉ ገጽታ አሳታፊ የማስተማር ዘዴን ለማከናወን አመቺ ነው? | 0 | 0 | 12 | 100 | 12 |
| 1.4. | በመቀመጫዎቹ መካከል በቂ የመተላለፊያ ቦታ አለ? | 5 | 41.6 | 7 | 58.4 | 12 |
| 1.5. | በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ብዛታቸው ተገቢ ነው? | 0 | 0 | 12 | 100 | 12 |
| 1.7. | መቀመጫዎች የተደረደሩት በቅደም ተከተል ነው? | 12 | 100 | 0 | 0 | 12 |
| 4.1. | ትምህርቱን የሚደግፉ የተለያዩ ስዕሎች ፣ ፖስተሮች ፣ ሰንጠረዦች ወዘተ... በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ አሉ? | 0 | 0 | 12 | 100 | 12 |

ከፍ ሲል በሰንጠረዥ አስር ላይ የተመለከተው ከአጥኚው የምልከታ ቅጽ የተገኙ ለተማሪ-ተኮር ትግበራ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ናቸው። ከጥያቄዎቹ ትይዩ የተገለጸው አሀዛዊ መረጃ አጥኚው በአስራ ሁለት የመማሪያ ክፍሎች ምልከታ በሚያደርግበት ወቅት ያገኛቸው ናቸው። ይህ በክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘው መረጃ በወቅቱ በክፍል ውስጥ የነበሩት ሁኔታዎች ለአቀራረቡ ትግበራ አመቺ መሆናቸውን ለመፈተሽ የቀረቡ ናቸው። ሆኖም ከመልከታው መረጃ እንደታየው  የሚከተሉት ነጥቦች  የአቀራረቡን ትግበራ ሊያደናቅፉ የሚችሉ ችግሮች ናቸው።

- በአብዛኛው ለክፍሉ ተማሪዎች በቂ የጠቀመጫ ወንበር አለመኖር
- የመቀመጫ ወንበሮቹ ተንቀሳቃሽ አለመሆን

- የመማሪያ ክፍሉ ገጽታ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመጠቀም አመቺ ያለመሆን
- የክፍል ጥበት
- በመቀመጫ ወንበሮች መካከል በቂ የመተላለፊያ ቦታ አለመኖር
- የመቀመጫ ወንበሮች አደራደር በመደዳ በመሆናቸው የቡድን ስራዎችን ለማሰራት አመቺ ያለመሆን
- ትምህርቱን የሚደግፉ የተለያዩ ስዕሎች ፣ ፖስተተሮች ፣ ሰንጠረገሮች ወዘተ የመርጃ መሣሪያዎች በመማሪያ ክፍሉ ውሰጥ አለመኖር

የሚሉ ናቸው።

ከተተኳሪ መምህራን በቃለ መጠይቅ አማካይነት የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል።

መምህር ሀ፦ የተማሪዎች የመሳተፍ ፍላጎት ማነስ አንዱ ችግር ነው። የተማሪዎች ፍላጎት ማነስ ብዙ ጊዜ የምቸገርበት ስለሆነ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ሌሎችም ችግሮች አሉ። ለምሳሌ፦ የተማሪዎች ብዛት ፣ የማስተማሪያ ክፍል ውስጥ የመቀመጫ አደረጃጀት፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎች አለመኖር በዋናነት የሚጠቀሱ ችግሮች ናቸው።

መምህር ለ፦ ይህ ብቻ እይደለም አቀራረቡን የሚያደናቅፉ በርካታ ችግሮች አሉ። የክፍል ጥበት፣ የመቀመጫ ወንበር እጥረት ፣ የመማሪያ መጽሀፍ እጥረት የመሳሰሉት ናቸው። የሰፊ ክፍል መኖር እንደልብ ተዟዙሮ ለመቃኘትና ለመቆጣጠር ስለሚያመች ነው። የመፅሀፍ መኖር ሁሉንም ተሳታፊ ለማደረግ፣ የወንበር እጥረት ያለመኖር ደግሞ ሁሉንም በነፃነት ለማሳተፍ ስለሚያስችል ነው።

መምህር ሐ፦ አሳታፊ የማስተማር ዘዴን በአግባቡ ለመተግበር ብዙ ሁኔታዎች መመቻቸት አለባቸው። ለምሳሌ፦

- የመማሪያ ክፍሉ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መሟላት አለበት።
- በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥራቸው መጠነኛ መሆን አለበት።

- መማሪያ ክፍሉ ተማሪዎችን በሚያሳትፍ መልኩ የተደራጀ መሆን አለበት።
- ተማሪዎች የመሳተፍ ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል። የእነዚህ ሁኔታዎች ያለመመቻቸት ችግሮች ናቸው።

መምህር መ፦ - በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር መብዛት

- የመማሪያ ክፍል አለመመቻቸት
- የመቀመጫ እጥረት
- የመምህራን እጥረት
- የትምህርት መርጃ መሣሪያዎቸ ተሟልተው ያለገኘት ወዘተ ናቸው።

መምህር ሠ፦ የተማሪ-ተኮር ትግበራን የሚያደናቅፉ በርካታ ችግሮች አሉ። ለምሳሌ፦ የተማሪዎች ብዛት ፣ ተማሪዎች ለአቀራረቡ ያላቸው አመለካከት ጥሩ ያለመሆን ማለትም ተማሪዎች በትምህርቱ እንዲሳተፉ በምታደረግበት ጊዜ ዝግጅት ሳያደረግ ስለመጣ ነው ወይም በቂ ዕውቀት ስለሌለው ነው ብለው ያስባሉ። ሌላው የጊዜ እጥረት ነው።

መምህር ረ፦ አሳታፊ ዘዴዎችን ለመተግበር የሚያቸግሩ ብዙ መሰናክሎች አሉ። እነዚህም የጊዜ እጥረት ፣ በአብዛኛው ተማሪዎች ለመሳተፍ ያላቸው ፍላጎት አናሳ መሆን፣ የክፍል አደረጃጀት ፣ የተማሪዎች ብዛት ፣ የመማሪያ መጻሕፍት ያለመዳረስ የመሳሰሉት ናቸው።

ሌላው አጥኚው የክፍል ውስጥ ምልከታ በሚያደርግበት ወቅት የአቀራረቡን ትግበራ ሊያደናቅፉ የሚችሉ ችግሮችን ተመለከቷል። ይህም በሚከተለው ሰንጠረዥ የተመለከተው ነው።

በአጠቃላይ በጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለጊዜ ያለውን የተማሪ-ተኮር አተገባበር ሊያደናቅፉ የሚችሉ በርካታ ችግሮች አሉ። እነዚህም የጊዜ እጥረት ፣ የማመሪያ ክፍል ጥበት ፣ የተማሪዎች ብዛት ፣ የመማሪያ ክፍሎች አደራጀጀት አመቺ አለመሆን ፣ የተማሪዎች የተሳትፎ ፍላጎት ማነስ ፣ የመማሪያ መፅሀፍት እጥረት እንዲሁም በመማሪያ ክፍል ውስጥ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተሟልቶ አላመገኘት ናቸው።

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የመፍትሔ ሃሳብ

## 5.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በካፋ ዞን በተመረጡ ሶስት የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ እና 10ኛ) ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡ዝርዝር አላማዎቹም በካፋ ዞን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ምን ያህል እየተጠቀሙ እንደሚገኙ መለየት ፣ ተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብን ሊያደናቅፍ የሚችሉ ችግሮችን መለየት እንዲሁም ችግሮቹን ለመቅረፍ የሚያስችሉ የመፍትሔ ሃሳቦችን መጠቆም የሚሉ ናቸው፡፡

በትምህርት ቤቶቹ የአቀራረቡን ትግበራ ለመፈተሽ በትምህርት ዘመኑ ካሉት የዘጠነኛና የአስረኛ የክፍል ደረጃዎች ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት አራት አራት ምድቦች ተመርጠው በጥናቱ ተካተዋል። በእነዚህ ምድቦች ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንም በጥናቱ ታቅፈው በሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በመታገዝ ከተገኘው ውጤት በመነሳት ከዚህ በታች ከቀረቡት ድምዳሜዎች ላይ ለመድረስ ተችሏል።

- በትምህርት ቤቶቹ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች በቡድን ውስጥ ሁሉም የቡድኑ አባላት እኩል አይሳተፍም፣ ጥያቄ የሚጠይቁም ሆነ የሚመልሱ ተማሪዎች ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ብቻ ናቸው፡፡
- በትምህርት ቤቶች መምህራን ከተማሪ ተኮር አቀራረብ ጋር በተያያዘ ሚናቸውን አልተወጡም፡፡ ማለትም ለተማሪዎቻቸው የትምህርታቸውን ርዕስ ቢያስተዋውቁም የትምህርቱን አላማ አይገልፅም፣ ተማሪዎችን ከትምህርቱ በፊት እንዲነቃቁ አያደርጉም፣ ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት የሚኖራቸውን ሚና አይገለፁም፡፡
- የትምህርት ቤቶቹ ተማሪዎች በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በቡድን ውይይት ወቅት ሁሉም የቡድን አካላት የየራሳቸው የሆነ አስተባባሪነት፣ የፀሃፊነት፣ የጊዜ

ተቆጣጣሪነት፣ የአቅራቢነት ሚና አልተሰጣቸውም:: ተማሪዎች የሚማሩትን ነገር እንዲሁም የሚለማመዱበትን ነገር የመምረጥ እድል የላቸው::

- በትምህርት ቤቶቹ መምህራን ገላፃን በማስተማሪያነት አዘውትረው ይጠቀማሉ::
- የትምህርት ቤቶቹ የመማሪያ ክፍሎች አደረጃጀት የተማሪዎች የመቀመጫ አደራደር በመደዳ ሲሆን ተንቀሳቃሽ አይደሉም::
- በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ተግባራዊ ለማድረግ ከሚያጋጥሙ ችግሮች መካከል፣ የክፍል ጥበት፣ በቡድን ወይይት ጊዜ ሁሉም የቡድን አባላት እኩል ተሳትፎ ያለማድረግን የትምህርት ግብዓትና የጊዜ እጥረት ናቸው::

## 5.2. የመፍትሔ ሃሳቦች

ከላይ በማጠቃለያው የቀረቡትን ድምዳሜዎች ስንመለከት በተተኳሪ ትምህርት ቤቶቹ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ያለው የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ጥሩ አይደለም ማለት ይቻላል። በመሆኑም አቀራረቡ ለቋንቋ ትምህርት ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ስለሆነ አሁን ካለበት ሁኔታ መሻሻልና ጥሩ ደረጃ ላይ መድረስ እንዳለበት ይታመናል። ስለዚህ ከዚህ በማስቀጠል ለችግሩ የመፍትሔ ሃሳቦች ይሆናሉ ተብለው የታመነባቸው ነጥቦች ሰፍረዋል።

- ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች ቀዳሚ ሚና የሚሰጣቸው ናቸው:: ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው ባለው የትምህርቱ ሂደት ተማሪዎች በቀዳሚነት ይሳተፋሉ:: በትምህርታቸውም ሂደት ውስጥ በዋናነት ሲሳተፉ ሃላፊነትን ይወስዳሉ። ይህም ለእውቀታቸውና ለትምህርታቸው ውጤት በግል እንዲተጉ ያደርጋቸዋል:: ከዚህ አንፃር በካፋ ዞን ባሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የሚማሩትንና የሚለማመዱበትን ነገር በመምረጥ እንዲሁም ተነሳሳሽነትን በመፍጠር ረገድ እንዲሳተፉ ቢደረግ፣
- ተማሪዎች በቡድን ውይይት ጊዜ የቡድኑ አባላት እኩል ተሳታፊ የሚሆኑበት፣ ሃሳቦችን በነፃነት የመግለፅ ልምድና እንዲሁም ክሂሎቻቸውን የሚያዳብሩበት ሁኔታ ቢመቻች፤
- የመማሪያ ክፍሎች አደረጃጀት ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ከፍተኛ አስተዋፆኦ አላቸው:: በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ቡድኖችን በማደራጀት ከቦታ ቦታ

ለመንቀሳቀስ፣ ተማሪዎች ፊት ለፊት እየተያዩ ሀሳባቸውን እንዲለዋወጡ ለማድረግ የመቀመጫ ወንበሮች ተንቀሳቃሽና በመካከላቸው ለመተላለፊያነት በቂ ቦታ ያላቸው ቢሆኑ፣

- የቡድን ውይይት ውጤታማ የሚሆነው ሁሉም የቡድን አባላት በተመጣጣኝ ደረጃ ሲሳተፉ ነው፡፡ በመሆኑም መምህራን ይህንን ተረድተው በቡድን ውይይት ወቅት ለተማሪዎች ሚና ለይተው ቢሰጡ እና ሚናቸውን መወጣታቸውን ቢቆጣጠሩ፡፡
- የመማር ማስተማር ሂደቱን ተጨባጭ ለማድረግ የትምህርት ግብዓቶች መሟላት መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ የሚመለከተው አካል ይህንን ተረድቶ የተለያዩ የትምህርት መሳሪያዎችን ለማዘጋጀት የሚረዱ ግብዓቶች ቢያቀርብ፣ የሚሉ የመፍትሂ ሃሳቦች የቀረቡ ቢሆንም ከላይ የቀረቡትን መፍትሄዎች ለታዩት ችግሮች ብቸኛ ባለመሆናቸው የዞኑ ትምህርት ቢሮ፣ የወረዳው የትምህርት መምሪያ፣ ትምህርት ቤቶች፣ ትምህርት ክፍሉና የትምህርት ክፍሉ መምህራን ሌሎች አመራጭ መፍትሔዎችን ካሉበት ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ሊጠቀሙ እንደሚገባ ይታመናል፡፡

# ዋቢ ጽሁፎች

ኤልያስ አድማሱ፡፡ 1997 ፡፡ "በኦሮሚያ መምህራን ኮሌጅ ውስጥ መሰረታዊ አማርኛን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ አቀራረብ ፍተሻ፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ለኤም.ኤ.ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ፡፡ ያልታተመ፡፡

ሙሉጌታ ይታየው፡፡ 1996 ፡፡ "የተማሪ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፤ ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሰርተፍኬት መርሃ ግብር እንደታየው፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ለኤም.ኤ.ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ፡፡ ያልታተመ፡፡

ደረጀ ነጋሽ፡፡ 1999 ፡፡ "የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር ፍተሻ በደብረማረቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ አማርኛ ትምህርት ክፍል (10+3) መርሃ ግብር፡፡" አዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፡፡ ያልታተመ፡፡

ትምህርት ሚኒስተር፡፡ 1994 ፡፡ የትምህርት መስፋፋትና ጥራት ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው ለመምህራንና ለርዕሳነ መምህራን በተዘጋጀ አውደ ጥናት ላይ የቀረበ ፡፡ ያልታተመ፡፡

ያለው እንዳወቀ ፡፡ 2001፡፡ *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር*፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

አብዱራህማን መሃመድ፡፡1983 ፡፡ *መምህርና ስራው*፡፡ አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ.፡፡

Aggarwal, J.C.1996. *Principles, Methods and Techniques of Teaching*. New Delhi: S.n. Printers.

Bonwell, C and Elison, A. 2003. *Active Learning Creating Excitement in the Classroom*. Rhen: Grips.

Borich, G. 1988. *Effective Teaching Methods.* Columbus: Merlin Publishing Company.

Borich, G. D. 1984. *Effective Teaching Methods.* New York: Macmillan Publishing Company.

Brad, Hayes. 2000. *Teacher Centered Instruction Vs Student Centered Instruction: Armuchee High School.* New York: American Government Schools.

Calahan, J. et. al. 1988. *Teaching in the Middle Secondary Schools: Planning for Competence.* New York: Macmillan.

Capel, et. al. 1995. *Learning to Teach in the secondary Schools.* London: Rutledge.

Celce-Murcia. 1991. *Teaching English as a Second Language.* New York: Longman, Inc.

Chet, et al. 1993. *Promoting Active-learning Strategies for the College Classroom.* Sanfransisco: Jossey. Base 74.

Cruick Shank and Others.1999. *The Act of Teaching.* Boston: McGraw Hill Companies. Inc

Dickinson, L. 1987. *Self Instruction in Language Learning.* Cambridge: CUP.

Eggen, P.D and D.P. Kauchax. 1996. *Strategies for Teachers: Teaching Content and Thinking Skills.* Boston: Allyn and Bacon.

Fisseha Abera (2001). "Hampering Factors to Implement Active Learning in some Selected 2nd Cycle Primary Schools of Central zone of Tigray." Addis Ababa University School of Graduate Studies. Unpublished.

Garkns, R. and Redman, S. 1986. *Working With Words: A Guide to Teaching and Learning Vocabulary.* Cambridge: CUP.

ICDR. 1999. *Teacher Education Hand Book.* Addis Ababa: Finfine Printing.

Johnson B. and Johnson B. 1989. *Cooperative Learning: A New Direction in Education.* Oxford: OPU.

Kaplan. 1990. Psychology of Education for Tomorrows Teachers. London: Mc-Graws-hill

Krashen, S.D. 1987. Principles and Practices in Second Language Acquisition. UK: Printice Hall International.

Leu, E. (1998) "Designing Integrated Curriculum Materials for Primary Education." a Paper Presented at the Workshop in Oromia Education Bureau. Unpublished.

_________ .2000. "The Role of Curriculum Integration in Basic Education." Tigrai Education Bureau. Unpublished.

_________. 2000."The New Curriculum Issue of Theory and Practice for Teaching Education." Abbiyi Addi College of Teacher Education BESO Project. (Unpublished)

Lewy, A. 1979. *Hand Book of Curriculum Evaluation.* UNESCO Paris.76.

Littlewood, W. 1981. *Communicative Language Teaching.* Cambridge: Cambridge University Press.

Macharia, S. N. and Waria L.M. 1994. *Teaching Practice in Primary Schools.* Hong Kong: Macmillan Publishing Company.

McCombs, B.L. and Whisler, J.S. 1997. *The Learner Centered Classroom and School: Strategies for Increasing Students Motivation and Achievement.* Sanfrancisco: Jossey bas Publisher.

Moore, K. 2001. *Classroom Teaching Skills.* New York: McGraw Hill.

Mutassa, N.G. and Wills G.M. 1994. *Modern Practice in Education and Science.* Gaborone: Bostwana.

Nunan, D. 1989. "A Client Centered Approach to Teacher Development." *ELT Journal* 43/2

O'Hara, M. and O'Hara, J.A. 1998. *Cooperative Learning: A Paradigm for Learning in 21st Century American Secondary Education.* Boston: Allyn and Bacon.

Oskarsson, M. 1978. *Appropriate to self-Assessment in Foreign Language Learning.* Oxford: OUP.

Plass, H. 1998. "The Learner- Centered Classroom." In Amare Asgedom and et. al.(eds.). *Quality Education in Ethiopia Vision for 21st Century.* Addis Ababa University Press.

Reed, A. J. and Bergemann, V.E. 1995. *In the Classroom: An Introduction to Education.* (2nd ed.). North Carolina, Asheville: DPG Inc.

Richards, J. and Rodgers, C. 1986. *Approaches and Methods of Teaching Foreign Language.* Cambridge: CUP.

__________2001. *Approaches and Methods in Teaching Foreign Language.* Cambridge: CUP.

Richards, J.C and Lockhart, C. 2000. *Reflective Teaching in Second Language Classroom.* (7th ed.). Cambridge: CUP.

Silberman, M. 1996. *Active Learning: 101 Strategies to Teach any Subject.* Boston: Allyn and Bacon.77

Squazzin, T. and Grann, M.V. 1998. *Education Reform and Innovations in Namibia.* Okahandja: Namibia.

Taye Geresu. 2008. "Perceptions and Practices of Active Learning in EFL Classes of Dilla University." Addis Ababa University School of Graduate Studies. Unpublished.

Tudor, I. 1996. *Learner Centeredness as a Language Education.* Cambridge: CUP.

http://www.honolulu,hawail.edu/intrant/teachtip.htm. (26/08/2010)

http://www.Secondaryschools.com/approach.html. (15/07/2010)

web.www.neiu.edu/dbehrile.hrd.408/glossary.htm. (23/08/2010).

## ሙያዊ ቃላት

ከተገኙበት ቋንቋ ተተርጉመው የአማርኛ ቋንቋ ፍቺ የተሰጣቸው ቃላት በጥናቱ ውስጥ ጥቅም ላይ ውለዋል፤ ስለዚህ ለአንባቢ የሚስተላልፉት ሀሳብ ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ ስያሜ ቃላቱን ከእንግሊዝኛ አቻቸው ጋር በፊደል ተራ ቅደም ተከተል በማስቀመጥ ትርጓሜያቸው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| | |
|---|---|
| Action Research | ተግባራዊ ምርምር |
| Active Learning | አሳታፊ ትምህርት |
| Active participant | ንቁ ተሳታፊ |
| Brainstroming | ማነቃቂያ |
| Case study | አጫጭር ጥናት |
| Cooperative learning | ትብብራዊ ትምህርት |
| Gap lecture | አሳታፊ ገለፃ |
| Creative Writing | የፈጠራ ጽሑፍ |
| Evaluating | መገምገም |
| Games | ጨዋታዎች |
| Group Writing | የቡድን ጽሑፍ |
| Jigsaw Group | የጂግሳው ቡድን |
| Pair discussion | የጥንድ ውይይት |
| Parsive listener | ለዘብተኛ አድማጭ |
| Peer teaching | የብጤ ማስተማር |
| Principle of cooperative learning | የትብብራዊ ትምህርት መርሆች |
| Refleciton | ዕብረቃ |
| Report writing | ዘገባ ማቅረብ |
| Role playing | የሚና ጨዋታ |

| | |
|---|---|
| Self-assesment | የግል ግምገማ |
| Story telling | ታሪክ መናገር |
| Student Centred Approach | ተማሪ-ተኮር አቀራረብ |
| Field Trip | የመስክ ጉዞ |

# አባሪዎች

## አባሪ ሀ

## ተማሪ-ተኮር የማስተማሪያ ዘዴዎች

- ትብብራዊ ትምህርት /Cooperative Learning/
- አሳታፊ ገለጻ /gap lecture/
- ፕሮጀክት
- ማሳየት /demonstration/
- ተግባራዊ ምርምር /Action research/
- መረጃ መሰብሰብ
- ዘገባ ማቅረብ
- የመስክ ጉዞ
- ቃለ መጠይቅ
- መመዝገብ
- ስዕል መሳል
- ማይንድ ማፕ / Mind map/
- ጥያቄና መልስ
- መገምገም
- በቡድን መፃፍ
- የቡድን ስራ
- አጫጭር ጥናት /Case study/
- ቻርቶችና ግራፎች
- ፖስተር መጠቀም
- ክርክር
- የቃላት ጨዋታ
- ሚና ጨዋታ
- ድራማ

- ገለጻን መተንተን
- ተግባቦት መፍጠር
- አንብቦ ማብራራት
- ማንበብና ማነጻጽር
- የጥንድ ውይይት
- በንቃት ማዳመጥ
- ትብብራዊ ትምህርት
- የግል ስራ
- ምርመራ
- ታሪክ መናገር /story telling/
- የቤት ስራ
- የክፍል ስራ
- የግል ግምገማ /self assessment
- የአቻ ማስተማር /Peer teaching/
- ጨዋታዎች/games
- የጂግሳው ቡድን
- ማነቃቂያ /brainstorming/
- የፈጠራ ፅሁፍ
- ውድድሮች
- የስዕል ትንተና
- ፅብረቃ /reflection/ እና ሌሎች ናቸው።

# አባሪ ለ

## የፅሁፍ መጠይቅ (በተማሪዎች የሚሞላ)

ይህ መጠይቅ የተዘጋጀው በተግበራዊ ስነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ ለማዘጋጀት የሚረዳ መረጃ ለመሰብሰብ ታስቦ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ በታች በዝርዝር ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በመስጠት የጥናቱን ስራ የተሟላ ለማድረግ ለምታደርጉልኝ እገዛ በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

አጠቃላይ መመሪያ፡-

መጠይቁ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ አንደኛው ክፍል አምስት አማራጮችን የያዘ የምርጫ ጥያቄ ሲሆን በሰንጠረዡ ውስጥ ከጥያቄው በትይዩ ከሚገኙት አማራጮች (✓) ምልክት በማስቀመጥ ምላሻችሁን አመልክቱ፡፡

ምርጫዎቹን፡- 5 = በጣም እስማማለሁ  4 = እስማማለሁ

3 = መወሰን ያስቸግረኛል  2 = አልስማማም

1 = ፈፅሞ አልስማማም

በሁለተኛው ክፍል ደግሞ አጭርና ግልፅ መልስ የሚያሹ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ከእነዚህ ጥያቄዎች አንፃር ያላችሁን ሀሳብ ስሜታችሁን ሳትደብቁ እንድትገልፁ እጠይቃለሁ፡፡

በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡

የትምህርት ቤቱ ስም ______________________________

ፆታ፡- ወንድ ☐  ሴት ☐

የክፍል ደረጃ 9ኛ ☐  10ኛ ☐

ምድብ/ ሴክሽን ____________

| ተ. ቁ. | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 1 | በተማሪ ተኮር አቀራረብ የቋንቋ ትምህርት እየተማርን እንገኛለን፡፡ | | | | | |
| 2 | በተማሪ ተኮር አቀራረብ የቋንቋ ትምህርት መማር ያስደስታል፡፡ | | | | | |
| 3 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሰራውን ልምምድ የመምረጥ እድል አላቸው፡፡ | | | | | |
| 4 | ተማሪዎች ንግግር፣ ውይይትና ክርክር ለማድረግ የሚያስችሉ ርዕሶችን | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በነፃነት ይመረጣሉ። | | | | | |
| 5 | የክፍል ውስጥ ልምምዶች ሙሉ በሙሉ በመምህራን የሚዘጋጁ ናቸው። | | | | | |
| 6 | ትምህርታችሁን በተግባር አስደግፋችሁ ትማራላችሁ። | | | | | |
| 7 | ከክፍል ልምምድ በኃላ ከመምህራችሁ ማበረታቻ፣ ምጋቤ ምላሽ (Feedback) ታገኛላችሁ። | | | | | |
| 8 | ትምህርታችሁን በአብዛኛው ከዕለት ተዕለት ህይወታችሁ ጋር ታገናኛላችሁ። | | | | | |
| 9 | የትምህርት ተግባራትን በአብዛኛው በቡድን ታከናውናላችሁ። | | | | | |
| 10 | በቡድን ውስጥ ሁላችሁም የየራሳችሁ ሚና (የፀሀፊነት፣ የአስተባባሪነት፣ የጊዜ ተቆጣጣሪነት) ይሰጣችኋል። | | | | | |
| 11 | ትምህርታችሁን ከመጀመራችሁ በፊት መቀስቀሻ (ማነሳሳሻ) ታገኛላችሁ። | | | | | |
| 12 | በቡድናችሁ ውስጥ ሁላችሁም በእኩል ደረጃ ትሳተፋላችሁ። | | | | | |
| 13 | ከአካባቢያችሁ ተጨባጭ ሁኔታና ከህይወታችሁ ጋር አያይዛችሁ የምትሰሯቸው መልመጃዎች በብዛት ይሰጧችኋል። | | | | | |
| 14 | በትምህርታችሁ መሠረት የአካባቢያችሁን ችግር ለመፍታት ትጥራላችሁ። | | | | | |
| 15 | የተለያዩ ይዘቶች ላይ በመዘጋጀት እርስ በርሳችሁ ትማማራላችሁ። | | | | | |
| 16 | ያላችሁን የቋንቋ ክሂል ለማሳደግ በክፍል ውስጥ ተግባራትን በነፃነት ታከናውናላችሁ። | | | | | |
| 17 | ነገሮችን በእውን በማየት ከዛ ነገር ጋር ተያያዥነት ያለው ነገር ቀርቦ እያያችሁ ተምራችኋል። | | | | | |
| 18 | መምህሩ ለችግሮች ወዲያው መፍትሔ ከመስጠት እርስ በራሳችሁ እንድትረዳዱ እድል ሰጥቶአችኋል። | | | | | |
| 19 | የሚሰጣችሁ ትምህርት በቋንቋው የመጠቀም ችሎታችሁን አሳድጎላችኋል። | | | | | |
| 20 | መምህራችሁ በክፍል ውስጥ ያላችሁትን ተማሪዎች እያንዳንዳችሁ ያላችሁን ችሎታ ለይቶ ያውቃል። | | | | | |

## ክፍል ሁለት

1. ክፍል ውስጥ መምህራችሁ በአብዛኛው የሚጠቀማቸውን የማስተማሪያ ዘዴዎች በስማቸው ይዘርዝሩ።

2. በተማሪ ተኮር አቀራረብ የቋንቋ ትምህርቱን ስትማሩ ለምሳሌ በቡድን ወይይት፣ በጥንድ ስራ፣ በግል ስራ ጊዜ ያጋጠሟችሁ ችግሮች ዘርዝረው ይፃፉ።

3. በአጠቃላይ በተማሪ ተኮር አቀራረብ ላይ ያለዎትን አስተያየት በዝርዝር ያስፍሩ።

# አባሪ ሐ

## የምልከታ ቅጽ

የትምህርት ቤቱ ስም፦___________________

ሴክሽን፦___________________

ቀን፦___________________

ክፍለጊዜ፦___________________

ሰዓት፦___________________

| ተ.ቁ. | የምልከታ ዝርዝር | | |
|---|---|---|---|
| 1. | **የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ** | አዎ | አይደለም |
| 1.1. | ለሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች በቂ የመቀመጫ ወንበሮች አሉ? | | |
| 1.2. | መቀመጫዎቹ ተንቀሳቃሽ ናቸው? | | |
| 1.3. | የመማሪያ ክፍሉ ገጽታ አሳታፊ የማስተማር ዘዴን ለማከናወን አመቺ ነው? | | |
| 1.4. | በመቀመጫዎቹ መካከል በቂ የመተላለፊያ ቦታ አለ? | | |
| 1.5. | በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ብዛታቸው ተገቢ ነው? | | |
| 1.6. | በመማሪያ ክፍሉ የቡደን ስራ ይከናወንበታል? | | |
| 1.7. | መቀመጫዎች የተደረደሩት በቅደም ተከተል ነው? | | |
| 1.8. | የመማሪያ ክፍሉ በቂ ብርሃንና አየር አለው? | | |
| 2. | **የመምህሩ ተግባር** | አዎ | አይደለም |
| 2.1. | የዕለቱን ትምህርት ርዕስ ለተማሪዎች አስተዋውቋል? | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 2.2. | የዕለቱን ትምህርቱን ዓላማ ለተማሪዎች ገልጿል? | | |
| 2.3. | ተማሪዎችን ለተለያዩ ተግባራት አደራጅቷል? | | |
| 2.4. | ተማሪዎች በክፍለጊዜው የሚያከናወኗቸውን ተግባራት በግልጽ አሳውቋቸዋል? | | |
| 2.5. | ተማሪዎች ትምህርቱን በፍላጎትና በትኩረት እንዲከታተሉ አነሳስቷቸዋል? | | |
| 2.6. | የተለያዩ ተማሪዎችን የሚያሳትፉ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተጠቅሟል? | | |
| 2.7. | ለተማሪዎች የቡድን ስራ ሰጥቷቸዋል? | | |
| 2.8. | ተማሪዎች በቡድን ውስጥ እኩል እንዲሳተፉ ተከታተሏቸዋል? | | |
| 2.9. | የተማሪዎችን ግንዛቤና ክሂል ለማወቅ ጥያቄዎችን ጠይቋል? | | |
| 2.10. | መምህሩ ለተማሪዎች የቡድን ስራ ፣ የቤት ስራ ፣ ለመለማመጃ የሚሆኑ ጥያቄዎችን ሰጥቷቸዋል? | | |
| 2.11. | መምህሩ ራሱ ከመመለስ ይልቅ ተማሪዎች እንዲመልሱ በቂ ዕድል ሰጥቷቸዋል? | | |
| 2.12. | መምህሩ የተማሪዎችን ስራ አይቶ ገንቢ አስተያየት ሰጥቷቸዋል? | | |
| 3. | **የተማሪዎች ተግባር** | አዎ | አይደለም |
| 3.1. | ተማሪዎች በችግር ፈቺ ተግባራት ላይ ይሳተፋሉ? | | |
| 3.2. | ተማሪዎች ሚናዎችን ይጫወታሉ ወይም ይወጣሉ? | | |
| 3.3. | ተማሪዎች በቡድን ይወያያሉ? | | |
| 3.4. | ተነሳሶትን በመፍጠር ረገድ ተማሪዎች ድርሻ አላቸው? | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3.5. | ተማሪዎች በቡድን ውስጥ የስራ ድርሻ ተሰጥቷቸዋል? | | |
| 3.6. | የቡድን ውስጥ የስራ ድርሻቸውን በአግባቡ ተወጥተዋል? | | |
| 3.7. | ጥያቄዎችን ጠይቀዋል? | | |
| 3.8. | የቃል ጥያቄ ለመመለስ ሁሉም ተማሪዎች ተሳትፎ ያደርጋሉ? | | |
| 3.9. | ተማሪዎች በንቃት ይሳተፋሉ? | | |
| **4.** | **የመርጃ መሣሪያዎች መኖር** | አዎ | አይደለም |
| 4.1. | ትምህርቱን የሚደግፉ የተለያዩ ስዕሎች ፣ ፖስተሮች ፣ ሰንጠረዦች ወዘተ... በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ አሉ? | | |
| 4.2. | መምህሩ ከመማሪያ መጽሀፉ ውጭ ሌሎች የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ተጠቅሟል? | | |
| 4.3. | መምህሩ የተለያዩ ሀሳቦችን ፣ ግነዛቤዎችን ፣ ነጥቦችን በመርጃ ሰሣሪያዎች አስደግፎ አቅርቧል? | | |

## አባሪ መ

## ከክፍል ውስጥ ምልከታ ተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | የምልከታ ዝርዝር | አጠቃላይ ምልከታ | ምላሾች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አዎ | | አይደለም | |
| | | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 1. | የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ | | | | | |
| 1.1. | ለሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች በቂ የመቀመጫ ወንበሮች አሉ? | 12 | 4 | 33.3 | 8 | 66.7 |
| 1.2. | መቀመጫዎቹ ተንቀሳቃሽ ናቸው? | 12 | 1 | 8.3 | 11 | 91.7 |
| 1.3. | የመማሪያ ክፍሉ ገጽታ አሳታፊ የማስተማር ዘዴን ለማከናወን አመቺ ነው? | 12 | 0 | 0 | 12 | 100 |
| 1.4. | በመቀመጫዎቹ መካከል በቂ የመተላለፊያ ቦታ አለ? | 12 | 5 | 41.6 | 7 | 58.4 |
| 1.5. | በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ብዛታቸው ተገቢ ነው? | 12 | 0 | 0 | 12 | 100 |
| 1.6. | በመማሪያ ክፍሉ የቡድን ስራ ይከናወንበታል? | 12 | 12 | 100 | 0 | 0 |
| 1.7. | መቀመጫዎች የተደረደሩት በቅደም ተከተል ነው? | 12 | 12 | 100 | 0 | 0 |
| 1.8. | የመማሪያ ክፍሉ በቂ ብርሃንና አየር አለው? | 12 | 12 | 100 | 0 | 0 |
| 2. | የመምህሩ ተግባር | | | | | |
| 2.1. | የዕለቱን ትምህርት ርዕስ ለተማሪዎች አስተዋውቋል? | 24 | 20 | 83.3 | 4 | 16.7 |
| 2.2. | የዕለቱን ትምህርቱን ዓላማ ለተማሪዎች ገልጿል? | 24 | 1 | 4.1 | 23 | 95.9 |
| 2.3. | ተማሪዎችን ለተለያዩ ተግባራት አደራጅቷል? | 24 | 0 | 0 | 24 | 100 |
| 2.4. | ተማሪዎች በክፍለጊዜው የሚያከናወኗቸውን ተግባራት በግልጽ አሳውቋቸዋል? | 24 | 0 | 0 | 24 | 100 |
| 2.5. | ተማሪዎች ትምህርቱን በፍላጎትና በትኩረት እንዲከታተሉ አነሳስቷቸዋል? | 24 | 1 | 4.1 | 23 | 95.9 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.6. | የተለያዩ ተማሪዎችን የሚያሳትፉ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተጠቅሟል? | 24 | 5 | 20.8 | 19 | 79.2 |
| 2.7. | ለተማሪዎች የቡድን ስራ ሰጥቷቸዋል? | 24 | 3 | 12.5 | 21 | 87.5 |
| 2.8. | ተማሪዎች በቡድን ውስጥ እኩል እንዲሳተፉ ተከታትሏቸዋል? | 24 | 1 | 4.1 | 23 | 95.9 |
| 2.9. | የተማሪዎችን ግንዛቤና ክሂል ለማወቅ ጥያቄዎችን ጠይቋል? | 24 | 16 | 66.6 | 8 | 33.4 |
| 2.10. | መምህሩ ለተማሪዎች የቡድን ስራ ፣ የቤት ስራ ፣ ለመለማመጃ የሚሆኑ ጥያቄዎችን ሰጥቷቸዋል? | 24 | 11 | 45.8 | 13 | 54.2 |
| 2.11. | መምህሩ ራሱ ከመመለስ ይልቅ ተማሪዎች እንዲመልሱ በቂ ዕድል ሰጥቷቸዋል? | 24 | 2 | 8.3 | 22 | 91.7 |
| 2.12. | መምህሩ የተማሪዎችን ስራ አይቶ ገንቢ አስተያየት ሰጥቷቸዋል? | 24 | 10 | 41.7 | 14 | 58.3 |
| 3. | የተማሪዎች ተግባር | | | | | |
| 3.1. | ተማሪዎች በችግር ፈቺ ተግባራት ላይ ይሳተፋሉ? | 24 | 0 | 0 | 24 | 100 |
| 3.2. | ተማሪዎች ሚናዎችን ይጫወታሉ ወይም ይወጣሉ? | 24 | 0 | 0 | 24 | 100 |
| 3.3. | ተማሪዎች በቡድን ይወያያሉ? | 24 | 3 | 12.5 | 21 | 77.5 |
| 3.4. | ተነሳሶትን በመፍጠር ረገድ ተማሪዎች ድርሻ አላቸው? | 24 | 0 | 0 | 24 | 100 |
| 3.5. | ተማሪዎች በቡድን ውስጥ የስራ ድርሻ ተሰጥቷቸዋል? | 24 | 0 | 0 | 24 | 100 |
| 3.6. | የቡድን ውስጥ የስራ ድርሻቸውን በአግባቡ ተወጥተዋል? | 24 | 1 | 4.1 | 23 | 95.9 |
| 3.7. | ጥያቄዎችን ጠይቀዋል? | 24 | 15 | | 9 | |
| 3.8. | የቃል ጥያቄ ለመመለስ ሁሉም ተማሪዎች ተሳትፎ ያደርጋሉ? | 24 | 0 | 0 | 24 | 100 |
| 3.9. | ተማሪዎች በንቃት ይሳተፋሉ? | 24 | 0 | 0 | 24 | 100 |
| 4. | የመርጃ መሣሪያዎች መኖር | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 4.1. | ትምህርቱን የሚደግፉ የተለያዩ ስዕሎች ፣ ፖስተሮች ፣ ሰንጠረዦች ወዘተ... በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ አሉ? | 12 | 0 | 0 | 12 | 100 |
| 4.2. | መምህሩ ከመማሪያ መጽሀፉ ውጭ ሌሎች የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ተጠቅሟል? | 24 | 2 | 8.3 | 22 | 91.7 |
| 4.3. | መምህሩ የተለያዩ ሀሳቦችን ፣ ግነዛቤዎችን ፣ ነጥቦችን በመርጃ ሰሣሪያዎች አስደግፎ አቅርቧል? | 24 | 2 | 8.3 | 22 | 91.7 |

## አባሪ ሠ

ለተተኩዋሪ መምህራን  የቀረቡ የቃለመጠይቅ ጥያቄዎች

1) አሳታፊ የማስተማር ዘዴን የሚመለከት ስልጠና ወስደው ያውቃሉ?
2) አሳታፊ የማስተማር ዘዴን በአብዛኛው በክፍል ውስጥ ተጠቅመዋል?
3) የተጠቀሟቸው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች የትኞቹ ናቸው?
4) በትግበራው ሂደት የገጠመዎት ችግር ምን ምንድን ነበር?

## አባሪ ረ

ከመምህራን ጋር ከተደረጉት ቃለመጠይቆች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

ቀጥሎ የቀረበው ቃለመጠይቅ ከመምህርት አዲስ አለም ጋር የተደረገው ነው።

አጥኚው፦ በመጀመሪያ ለዚህ ቃለመጠይቅ መለስ ለመስጠት ፍቃደኛ ስለሆንሽ ምስጋናዬ የላቀ ነው።

አዲስ፦ እኔም አመሰግናለሁ።

አጥኚው፦ አሳታፊ የማስተማር ዘዴን የሚመለከት ስልጠና ተሰጥቷችሁ ያውቃል?

አዲስ፦ ከዚህ በፊት ትምህርት ቤት /ካምፓስ/ ስለማስተማሪያ ዘዴዎች ስማር ተምሬ ነበር። ነገር ግን ስራ ከጀመርኩ ወዲህ የማጠናከሪያ ስልጠና ተሰጥቶኝ አያወቅም።

አጥኚው፦ ስለአቀራረቡ ያለሽ ግንዛቤ ምን ያህል ነው?

አዲስ፦ ከዚህ በፊት ዩኒቨርሲቲ እየተማርኩ የማስተማር ዘዴን በሚመለከት ኮርሶችን ወስጄ እንደነበር ግሬሃለሁ። ከዚያም በተጨማሪ የማስተማር ልምምድ ሳደርግ ከአማካሪዎቼ የወሰድኩትም ግንዛቤ አለ።

አጥኚው፦ ስለዚህ ያለኝ ግንዛቤ በቂ ነው ትያለሽ?

አዲስ፦ በስራ ሂደት በየጊዜው የሚሰጥ ስልጠና ቢኖር የተሻለ ነበር። ምክንያቱም ያለህ ነገር ውስን ሊሆን ስለሚችል በየጊዜው ግብአት ማግኘት የግድ ነው። ይህንን ለማግኘት ደግሞ ስልጠና ማግኘት የተሻለ ነው። ስለዚህ በየጊዜው ስልጠና ቢሰጥ የተሻለ ነው እላለሁ።

አጥኚው፦ በማስተማር ሂደት አሳታፊ የማስተማር ዘዴዎችን ትጠቀሚያለሽ?

አዲስ፦ አዎ ብቻ… በተወሰነ መልኩም ቢሆን እየተተጠቀምኩ ነኝ ማለት እችላለሁ።

ምክንያቱም አሳታፊ የማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂል ለማዳበር አጅግ አስፈላጊ እንደሆነ አውቃለሁ።

አጥኚው፦ በአብዛኛው የተጠቀምሻቸው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች የትኞቹ ናቸው?

አዲስ፦ በአበዛኛው የተጠቀምኳቸው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ቃላዊ ጥያቄ ፣ አሳታፊ ገለጻ ፣ የቡድን ስራ ፣ የቤት ስራ ብዙ ጊዜ የምጠቀማቸው ዘዴዎች ናቸው።

አጥኚው፦ አሳታፊ ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ ስትጠቀሚ የገጠመሽ ችግር አለ?

አዲስ፦ አሳታፊ የማስተማር ዘዴን በአግባቡ ለመተግበር ብዙ ሁኔታዎች መመቻቸት አለባቸው።

ለምሳሌ፦

- የመማሪያ ክፍሉ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መሟላት አለበት።
- በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥራቸወ መጠነኛ መሆን አለበት፦
- መማሪያ ክፍሉ ተማሪዎችን በሚያሳትፍ መልኩ የተደራጀ መሆን አለበት።
- ተማሪዎች የመሳተፍ ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል። የእነዚህ ሁኔታዎች ያለመመቻቸት ችግሮች

አጥኚው፦ በጣም አመሰግናለሁ።

አዲስ፦ እኔም አመሰግናለሁ።

ቀጣዩ ቃለመጠይቅ ከመምህር ታገል ጋር የተደረገ ነው።

አጥኚው፦ አሳታፊ የማስተማር ዘዴን የሚመለከት ስልጠና አግኝተህ ታውቃለህ?

መምህር ታገል፦ መቼ? ስራ ከጀመርኩ በኋላ ነው ወይስ ትምህርት ላይ እያለሁ?

አጥኚው፦ ስራ ከጀመርክ በኋላ

ታገል፦ ስራ ከጀመርኩ በኋላ አሳታፊ የማስተማር ዘዴን የሚመለከት ምንም ዓይነት

ስልጠና አልወሰድኩም።

አጥኚው፦ በአሳታፊ የትምህርት አቀራረብ ላይ ያለህ ግንዛቤ መን ያህል ነው?

ታገል፦ አሳታፊ ወይም ተማሪ-ተኮር የሚባለው የማስተማር ዘዴ በተለይ ለቋንቋ ትምህርት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ እገነዘባለሁ። ይህ አቀራረብ ተማሪዎችን ለተለያዩ የቋንቋ ገጽታዎች እንዲጋለጡ ስለሚያደርግ ቋንቋውን ይማሩበታል። ይህ ሁኔታ ደግሞ የቋንቋን ትምህርት አላማ ከግብ ሊያደርስ የሚችል ነው። በመሆኑም ተማሪዎች ቋንቋን እንዲማሩ በአብዛኛው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ መቅረብ እንዳለበት እገነዘበባለሁ።

አጥኚው፦ በማስተማር ሂደት ውስጥ አሳታፊ የማስተማር ዘዴን ተጠቅመሀል?

ታገል፦ ቀደም ሲል እንደገለጽኩልህ ለአቀራረቡ የተሻለ ግንዛቤ አለኝ። ነገር ግን ይህንን ለመተግበር ያለው ሁኔታ አመቺ አይደለም። በሀሳብ ደረጃ ብቻ ነው። ክፍል ውስጥ እንደተመለከትከው ተማሪዎቹ አድርጉ የምላቸውን ነገር ለማድረግ ፍላጎት የላቸውም። ተነሳሽነት የላቸውም። ተማሪዎቹ በአብዛኛው ፣ ሙሉ በሙሉ ማለት እችላለሁ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ስለሆነ የተባሉትን ነገር ለማከናወን ይቸገራሉ።

አጥኚው፦ ተማሪዎች እንዲነሳሱ ማድረግ አይቻልም?

ታገል፦ በርግጥ ተማሪዎችን ለተሳትፎ በተላያዩ ሁኔታዎች ማነሳሳት ይቻላል። አንተም እንደ ተመለከትከው ተማሪዎቹ ንቁ ተሳታፊ የተለያዩ ጥረቶችን አድርጌያለሁ። ጥያቄ ጠይቄያቸው በፈቃደኝነት ለመመለስ እጃቸውን ያላወጡትን ተማሪዎች ከጥያቄው አንጻር ያላቸውን ግንዛቤ እንዲገልፁ አድርጌያለሁ። በተጨማሪም

ሁልጊዜ ተሳተፎ ዋጋ እንዳለው በመግለጽ እንዲሳተፉ አበረታትቻቸዋለሁ

አጥኚው፦ ከተማሪዎች የፍላጎት ማነስ ውጭ ሌላ የገጠመህ ችግር የለም?

አዲስ፦ የተማሪዎች የመሳተፍ ፍላጎት ማነስ አንዱ ችግር ነው። የተማሪዎች ፍላጎት ማነስ ብዙ ጊዜ የምቸገርበት ስለሆነ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ሌሎችም ችግሮች አሉ። ለምሳሌ፦ የተማሪዎች ብዛት ፣ የማስተማሪያ ክፍል ውስጥ የመቀመጫ አደረጃጀት ፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎች አለመኖር በዋናነት የሚጠቀሱ ችግሮች ናቸው።

አጥኚው፦ ስላደረግክልኝ ትብብር አመሰግናለሁ።

ታገል፦ እኔም አመሰግናለሁ።

ቀጥሎ የቀረበው ቃለመጠይቅ ከመምህር አስማማው ጋር የተደረገ ነው።

አጥኚው፦ አሳታፊ የትምህርት አቀራረብን የሚመለከት ስልጠና ስራ ከጀመርክ በኋላ ተሰጥቶህ ያውቃል?

አስማማው፦ ምንም ዓይነት ስልጠና አልተሰጠኝም።

አጥኚው፦ ስለተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ያለህ ግንዛቤ ምን ያህል ነው?

አስማማው፦ ስለአሳታፊ የትምህርት አቀራረብ በምማርበት ወቅት ብዙ ግንዛቤ አግኝቻለሁ። በመሆኑም በሃሳብ ደረጃ በቂ ግንዛባ እንዳለኝ እረዳለሁ። አቀራረቡ ለቋንቋ ትምህርት ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። በመሆኑም ከቋንቋ ትምህርት ግብ አንጻር ሲታይ በጣም ጠቃሚ ነው። በመሆኑም በዚህ አቀራረብ ተማሪዎች ተማሪዎች እንዲናገሩ ፣ እንዲያዳምጡ ፣ እንዲፅፉና እንዲያነቡ ስለሚያደርግ ቋንቋን በቀላሉ ይማራሉ ማለት ነው።

አጥኚው፦ በክፍል ውስጥ በአብዛኛው አሳታፊ ዘዴዎችን ትጠቀማለህ?

አስማማው፦ አዎ! በአብዛኛው ባይሆንም አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ።

አጥኚው፦ ቀደም ሲል ይህ ዘዴ በተለይ ለቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ገልጸህልኝ ነበር። ይህ ከሆነ ታዲያ ለምን አልፎ አልፎ ብቻ ትጠቀማለህ?

አስማማው፦ ሙሉ በሙሉ እንደፈለገከው ለማድረግ የሚወስኑ ችግሮች አሉ። በተለይ የጊዜ እጥረት ዋነኛው ነው። በሳምንት እኮ ሁለት ክፍለጊዜ ብቻ ነው ያለው።

አጥኚው፦ ሌላስ የገጠመህ ችግር የለም?

አስማማው፦ ይህ ብቻ አይደለም አቀራረቡን የሚያደናቅፉ በርካታ ችግሮች አሉ። የክፍል ጥበት፣ የመቀመጫ ወንበር እጥረት ፣ የመማሪያ መጽሀፍ እጥረት የመሳሰሉት ናቸው። የሰፊ ክፍል መኖር እንደልብ ተዟዙሮ ለመቃኘትና ለመቆጣጠር ስለሚያመች ነው። የመፅሀፍ መኖር ሁሉንም ተሳታፊ ለማደረግ ፣ የወንበር እጥረት ያለመኖር ደግሞ ሁሉንም በነፃነት ለማሳተፍ ስለሚያስችል ነው።

አጥኚው፦ እስኪ በአብዛኛው የተጠቀምክባቸውን የማስተማሪያ ዘዴዎች ጥቀስልኝ።

አስማማው፦ አብዛኛውን ጊዜ የምጠቀመው አሳታፊ ዘዴ የቃላዊ ጥያቄና መልስ ነው። ይህንንም የተጠቀምኩት ተማሪዎች በቁጥር በዛ ስለሚሉ ሌሎች ዘዴዎችን ለመጠቀም ስለሚያስቸግር ነው።

አጥኚው፦ አመሰግናለሁ!

አስማማው፦ ምንም አይደለም።

## ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የራሴ መሆኑንና በጽሑፍ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ተዛማጅ ጽሑፎችና መረጃዎች በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን በስሜና ፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም ________________ ፊርማ ________________

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ፣ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

አዲስ አበባ

ሰኔ 2003 ዓ.ም.